# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 020 መስከረም 20 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




eccs

የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ

ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.

የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ



Mob. 0911 225057/ 0989 343434

አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት





ፀደይ ባንክ (አ.ማ)

TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ

Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98

P.O.Box: 9630

E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com

Web: www.tsedeybank.org.et

Addis Ababa, Ethiopia


# የአፍሪካ ውክልና - በጸጥታው ምክር ቤት

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

ዜና ትንታኔ

በሰው ሠራሽ ቀውሶች፣ በአየር ንብረት ለውጥ እና በዕዳ ጫና እየተፈተነች የምትገኘው አፍሪካ እንደ ጸጥታው ምክር ቤትና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች በመሳሰሉ ተቋማት ውስጥ ተገቢ ውክልና አለመኖሩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ከሆነባት ሰነባብቷል።

በዚህም የተነሳ ከሰባት አስርት ዓመታት በላይ አፍሪካ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ ውክልና እንዲሰጣት ግፊት ሲደረግ ቆይቷል። ነገሩ አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም ነውና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ለአፍሪካ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ምንም አይነት ምላሽ ሳይሰጥ ዘመናት አልፈዋል።

አፍሪካ ለጥያቄዎቿ የሚሆን ምንም እንኳን ለረጅም ጊዜ ያለምላሽ ብትቆይም የመንግሥታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በነሃሴ ወር 2016 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ለአፍሪካ ቋሚ መቀመጫ እንዲሰጣት ጥሪ ካቀረቡበት ጊዜ አንስቶ ጉዳዩ ይበልጥ ትኩረት አግኝቷል።

ዋና ጸሐፊው የምክር ቤቱ አሰራርና በአባላት ስብጥሩ በፍጥነት ከሚለዋወጠው የዓለም ሥርዓት ጋር እኩል የሚራመድ አለመሆኑንም ተናግረዋል። ከአንድ ነጥብ ሦስት

**የአፍሪካ ውክልና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**



# ከጉባኤው ጎን ለጎን የኢትዮጵያን ጥቅሞች የሚያስጠብቁ ውይይቶች እየተካሄዱ ናቸው

**ዘላለም ግዛው**


አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በኒውዮርክ እየተካሄደ በሚገኘው 79ኛው የተመድ ጉባዔ ጎን ለጎን የኢትዮጵያን ጥቅሞች በሚያስጠብቁ፣ ሁለትዮሽን በሚያጠናክሩና በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና ደኅንነት ላይ ያተኮሩ ውይይቶች ከተለያዩ ሀገራት ጋር እያካሄደች እንደምትገኝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ።

ሚኒስቴሩ በድረ ገጹ፤ በኒውዮርክ እየተካሄደ ካለው ጉባዔ ጎን ለጎን የኢትዮጵያን ጥቅሞች ለሚያስጠብቁ ጉዳዮች ቅድሚያ በመስጠት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ውይይቶች እያካሄዱ እንደሚገኙ አስነብቧል።

አምባሳደር ታዬ ከዴንማርክ አቻቸው ላርስ ሎክ ራስምሰን ጋር ባደረጉት ውይይት ዴንማርክ የተመድ የጸጥታው ምክር ቤት አባል ሆና በመመረጧ ደስታቸውን ገልጸዋል። በወቅታዊ የአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች እና ኢትዮጵያ ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ ባላት ቁርጠኝነት ዙሪያ ገለጻ አድርገዋል።

ከተባበሩት አረብ ኤምሬቶች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ሼህ ሻክቡት ናህያን አል ናህያን ጋር በሁለትዮሽ እና በአፍሪካ ቀንድ ሰላም እና ደህንነት ዙሪያ መክረዋል።

**ከጉባኤው ጎን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**



መስፍን ጠገና

# መንፈስንም ጉልበትንም አዳሹ ልማት - በገላን አራብሳ

**አስቴር ኤልያስ**

ዜና ሐተታ

"ድካም ብጤ ሲሰማኝ ጉልበቴንም መንፈሴንም ለማደስ በሁለት ኩሬዎች መካከል አረፍ እላለሁ።" ይላል ወጣቱ አርሶ አደር መስፍን ጠገና። መስፍን፤ በኩሬው ውስጥ ብቅ ጥልቅ የሚሉትን ዓሳ እና ከኩሬው በላይ ድምጽ እያሰሙ የሚያዝናኑትን ጅግራዎችን ማየት ጉልበቱን እንደሚያበረታለት ይናገራል።

በቅጥር ግቢያቸው የሚታዩት ኩሬዎቹ ብቻ አይደሉም፤ በርከት ያሉ የንብ ቀፎችም ጭምር እንጂ። በርከት ያሉ ባህላዊ የንብ ቀፎዎችና ከ40 በላይ የሚሆኑ ዘመናዊ የንብ ቀፎዎች በአግባቡ ተሰድረው ይስተዋላሉ። ጅግራዎቹም ቢሆኑ ከውበታቸው ባሻገር ኩሳቸው ለዓሳ ምግብነት፤ እንቁላላቸውና

**መንፈስንም ጉልበትንም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**


ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ

AMG Steel Factory



Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565


እጸገነት መንግስቱ

# ብልሹ አሠራሮችን በመቅረፍ የተፋጠነ ፍትህ ለመስጠት እየተሠራ ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በፍትህ ዘርፉ የሚስተዋሉ ብልሹ አሠራሮችን በመቅረፍ ሕብረተሰቡ የተፋጠነ የፍትህ አገልግሎት እንዲያገኝ በፍርድ ቤቶች የለውጥ ፍኖተ ካርታ ውስጥ ተካትቶ እየተሠራ እንደሚገኝ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ገለጸ፡፡

በምክር ቤቱ የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እጸገነት መንግስቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የፍትህ ሥርዓቱን በማዘመን፣ ሕዝቡ የሚፈልገውን የፍትህ ሥርዓት ዘመናዊና የተፋጠነ ለማድረግ እየተሠራ ነው፡፡

ሕዝቡ በአካባቢው ባሉ የፍትህ ተቋማት የተፋጠነ ፍትህ እንዲያገኝ፣ አቅም ያላቸው የፍትህ ተቋማት አመራሮች እና ባለሙያዎች እንዲፈጠሩ የለውጥ ፍኖተ ካርታው ውስጥ መካተቱንም አንስተዋል፡፡

በፍርድ ቤቶች ቴክኖሎጂን በመጠቀም ችሎቶችን ዲጂታላይዝድ በማድረግ ስማርት ኮርት የመፍጠር ተግባር ሰፋፊ ችግሮችን መቅረፍ የሚቻልበት መሆኑ ታምኖበታል ብለዋል፡፡

በፍርድ ቤቶች የግለሰብ ሰነዶች ባግባቡ መያዝ እንዳለባቸው እና የአንድ መዝገብ መጥፋት ቀላል ነገር እንዳልሆነ የገለጹት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢዋ፤ የዲጂታል ሥራ የተጀመረ በመሆኑ በቴክኖሎጂ ተደግፎ ከተሠራ ግለሰቦችን መጉዳትም ሆነ አላስፈላጊ ጥቅም ለማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ አይኖርም ነው ያሉት፡፡

የፍርድ ቤቶች የለውጥ ፍኖተ ካርታ ውስጥ ከተካተቱ ሰባት ምሰሶዎች የፍርድ ቤቶች ነጻነትና ተጠያቂነት ይገኛል፡፡ ተጠያቂነትን ማስፈን የሚቻልበት ሁኔታ በስፋት የሚተነትን መፍትሔ ተቀምጧል ሲሉም አክለዋል፡፡

የዳኞች፣ የተቋም እና የፋይናንስ ነጻነት መኖሩን እንዲሁም በርካታ ዝርዝር ጉዳዮች መካተታቸውን ጠቁመው፤ ዳኛው ነጻነቱ ተጠብቆለት ያለማንም ጣልቃ ገብነት ኃላፊነቱን እንዲወጣ፣ የተሰጠ እንጂ ግለሰብ እንደፈለገ የሚጠቀምበት ሥርዓት የሚፈጥር አይደለም ብለዋል፡፡

እንደ እጸገነት ገለጻ፤ በየመዋቅሩ ያሉ ዳኞችን በማሰልጠን አቅማቸውን መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ሕግን መሠረት በማድረግ የፍትህና የሕግ ኢንስቲትዩት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲሆን እየተሠራ ይገኛል፡፡

አመራሩንና ዳኞችን የማጥራት ሥራ እንደሚሠራ የጠቆሙት ወይዘሮ እጸገነት፤ የአቅም ችግር ያለበት በሚመጥነው ቦታ እንዲሠራ፣ በስልጠና አቅሙ ዳብሮ መሥራት የሚችለው አቅሙ እንዲገነባ ማድረግም የለውጥ ፍኖተ ካርታው አካል ሆኖ እየተተገበረ ይገኛል ብለዋል፡፡

ክልሎች ሀገራዊ ሰነዱን መነሻ በማድረግ ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በሚስማማ መልኩ ሰነዱን በማዘጋጀት ማቀዳቸውንም አመልክተዋል፡፡

አያይዘውም በፍርድ ቤቶችና በፍትህ ተቋማት ያለው ስብራት ሰፊ ጊዜና ብዙ ሥራ ይጠይቃል። በአንድ ጊዜ ውጤት ማምጣት የሚቻልበት ደረጃ ላይ አልተደረሰም፡፡ ተከራካሪዎች በፍርድ ቤት በሚሰጣቸው ውሳኔ ትክክል ነው ብለው የሚቀበሉበትን ሥርዓትም አልገነባንም ብለዋል፡፡

የሕዝቡን እርካታ ከፍ ማድረግ የሚቻለው በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በሳይንሳዊ ጥናት በመለየት በእያንዳንዱ የሥራ መዘርዝር ውስጥ ተካትቶ ሲሠራ መሆኑ ታምኖበት በእቅድ እየተከናወነ እንደሚገኝ እጸገነት ጠቁመዋል፡፡



# ልማቱ ነዋሪዎችን የዘመናዊ መኖሪያ ቤት ባለቤት ከማድረጉ ባሻገር በምቹ አካባቢዎች የመኖር ዕድልን ይፈጥራል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ልማቱ ነዋሪዎችን የዘመናዊ መኖሪያ ቤት ባለቤት ከማድረጉ ባሻገር ምቹ በሆኑ አካባቢዎች የመኖር ዕድልን የሚፈጥር ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የተገነቡ 75 መኖሪያ ቤቶችን መርቀው ለተጠቃሚዎች አስተላልፈዋል።

ከንቲባዋ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት የዘመሙ ጎጆዎችን እያቃናን የሚፈሱ እንባዎች ሲታበሱ ማየት እጅግ ደስ ያሰኛል ብለዋል።

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ዊንጌት እና ገብስ-ተራ አካባቢ ደሳሳ የሆኑ የቀበሌ ቤቶችን በማፍረስ ለመኖር ምቹ እና ለሰው ልጅ የሚመጥኑ 75 የመኖሪያ ቤቶች ያላቸው ባለ 5 ወለል(G+5) ሁለት ህንጻዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተገንብተው ለነዋሪዎች በትናንትናው ዕለት መተላለፋቸውን ገልጸዋል።

የተላለፉት ምቹና ፅዱ የመኖሪያ ቤቶች በመሃል


ከንቲባ አዳነች አቤቤ

ከተማ የተገነቡ፣ የመጸዳጃና የማብሰያ ቦታ እንዲሁም ሰፋፊ ክፍሎች ያላቸው ሆነው የተለወጡ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

ቤቶቹ ከዚህ ቀደም ለመኖር ቀርቶ በዚያ ለማለፍ እንኳን ይከብዱ የነበሩ መሆኑን ጠቁመው፤ የመኖሪያ ቤቶቹ ከቦታው ከተነሱ ነዋሪዎች በተጨማሪ ለልማት ከመኖሪያ አካባቢያቸው ለሚነሱ ዜጎች የሚተርፉ ሆነው በጥሩ ሁኔታ ተገንብተዋል ነው ያሉት።

ልማቱ ነዋሪዎቻችንን የዘመናዊ መኖሪያ ቤት ባለቤት እና ምቹ በሆኑ አካባቢዎች የመኖር እድልን የሚፈጥርላቸው መሆኑንም ገልጸዋል ከንቲባዋ በመልዕክታቸው።

ከንቲባዋ አክለውም ራዕያችንን በመጋራት ቤቶቹን ለመገንባት የደገፋችሁንና ያስተባበራችሁ አካላትን በሙሉ በተለይም የብዙአየሁ ታደለ ፋውንዴሽን፣ መተባበር ለኢትዮጵያ አክሲዮን ማህበር፣ ተምሳሌት በሲዳሞ ተራ አክሲዮን ማህበር፣ ምዕራብ ገበያ ልማት አክሲዮን ማህበር፣ ጉሊት አክሲዮን ማህበር፣ ሸራ ተራ ብርሃን አክሲዮን ማህበር እንዲሁም ጎሽ ንግድና አክሲዮን ግንባታ ማህበርን በተጠቃሚ ነዋሪዎች እና በከተማ አስተዳደራችን ስም ላመሰግናችሁ እወዳለሁ ብለዋል።

ስንተባበር የሰው ኑሮ እና አኗኗርን እያሻሻልን ሀገር እንገነባለንና ትብብራችንን አጠናክረን እንቀጥል ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል።

# በክልሉ ገጠራማ አካባቢዎች 190 ሺህ ዘመናዊ ምድጃዎች ሊሠራጩ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል የገጠሩን ማህበረሰብ ፍትሐዊ የኢነርጂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ 190 ሺህ የተሻሻሉ ዘመናዊ ምድጃዎችን ለማሰራጨት እየተሠራ መሆኑን የክልሉ ውሃና ኢነርጂ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአማራ ክልል የውሃና ኢነርጂ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ጥላሁን ሽመልስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2017 ዓ.ም በአማራ ክልል የገጠሩን ማህበረሰብ ፍትሐዊ የኢነርጂ ተጠቃሚ በማድረግ ጤንነቱ የተጠበቀ እና በኢኮኖሚ ያደገ ዜጋ ለመፍጠር በትኩረት እየተሠራ ነው፡፡

በተለይ የገጠሩ ማህበረሰብ ንፁህ ማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ማድረግ የእናቶችና የሕፃናትን ጤንነት ለመጠበቅ፣ ሴቶችን ከፆታዊ ጥቃት ለማዳን ከሚሰጠው ጥቅም በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማሳለጥ ትልቅ ፋይዳ አለው ብለዋል፡፡

ኢነርጂ የአንድ ሀገር ዕድገት ሞተር መሆኑን በመጥቀስ፤ ለሁለተናዊ ዕድገት ሞተር የሆነውን ኢነርጂ ለገጠሩ ማህበረሰብ በፍትሐዊ መንገድ ተደራሽ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በክልሉ ፍትሐዊ የኢነርጂ ተደራሽነትን በማስፈን ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማስመዝገብ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡

የክልሉ ማህበረሰብ ማገዶንና የእንስሳት ቅሪት አካልን ለማብሰያ እየተጠቀመ መሆኑን ጠቅሰው፤ ነዋሪው ጤንነቱን ለመጠበቅና ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱን ይበልጥ ለማሳደግ የተሻሻሉና ኃይል ቆጣቢ ንፁህ የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት ለገጠሩ ማህበረሰብ የተሻሻሉ ንፁህ የማብሰያ ቴክኖሎጂዎችንና ሶላር ኢነርጂዎችን ተደራሽ ለማድረግ በክልሉ አልፎ አልፎ የሚከሰተው የፀጥታ ችግር ትልቅ ፈተና እንደሆነባቸው ገልጸው፤ 116 ሺህ የተለያዩ ዘመናዊ ምድጃዎችን ተደራሽ የማድረግ ሥራ ተግባራዊ ተደርጓል ብለዋል፡፡

በመንግሥት አቅም ብቻ የገጠሩን ማህበረሰብ ፍትሐዊ የኢነርጂ ተጠቃሚ ማድረግ አይቻልም፤ ማህበረሰቡን በኢነርጂ ተጠቃሚ ለማድረግ የሶላር ቴክኖሎጂን ለህብረተሰቡ በበቂ ሁኔታ ተደራሽ ማድረግ የሚችሉ ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሳተፉ፤ ብዛት ያላቸው ባለሙያዎች እንዲሰማሩ የማበረታታት ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በክልሉ ኃይል ቆጣቢ ንፁህ ማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን የሚያመርቱ ወደ 80 የሚጠጉ ሴቶች እንዳሉ ጠቅሰው፤ ቴክኖሎጂዎች በስፋት እንዲያመርቱና ተደራሽ እንዲሆኑ ለአምራቾች የገበያ ትስስር የማመቻቸትና


አቶ ጥላሁን ሽመልስ

የመደገፍ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት 190 ሺህ የተለያዩ ንፁህ የማብሰያ ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም 190 ሺህ ሶላሮችን ለማህበረሰቡ ለማሰራጨት ሰፊ ሥራ እየተከናወነ ነው ያሉት አቶ ጥላሁን፤ እቅዱን ማሳካት ከተቻለ 190 ሺህ አባወራዎች ብቻ ሳይሆኑ በስራቸው የሚተዳደረው የቤተሰብ አባል ሁሉ ተጠቃሚ ይሆናል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# “ኢሬቻ ብዝሃ ማንነቶች፣ አብሮነታቸውንና ወንድማማችነታቸውን የሚያጎለብቱበት በዓል ነው”

## - አባ ገዳዎችና ሀዳ ሲንቄዎች

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ኢሬቻ በኢትዮጵያ የሚገኙ ብዝሃ ማንነቶች፣ አብሮነታቸውንና ወንድማማችነታቸውን የሚያጎለብቱበት በዓል ነው ሲሉ አባ ገዳዎችና ሀዳ ሲንቄዎች ገለጹ።

የኦሮሞ ቱለማ አባ ገዳ ጎበና ሆላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኦሮሞ ሕዝብ ክረምት አልፎ ፀደይ ሲመጣ፤ በክረምት ወራት ተራርቆ ሳይገናኝ የቆየ ዘመድ አዝማድ ሲገናኝ፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን ላሻገረው አምላክ ምስጋና የሚያቀርብበት በዓል ነው።

ኢሬቻ ምስጋና ብቻ ሳይሆን የአንድነት፣ የወንድማማችነት፣ የእርቅና የሰላም በዓልም መሆኑን ገልጸው፤ የኢሬቻ ቀን ከመድረሱ በፊት የተቀያየመ፣ የተጣላ ሁሉ ታርቆ፣ ይቅር ተባብሎ ቂም በቀልን አስወግዶ፤ በኢሬቻ ቀን ፈጣሪ (ዋቃ)ን በማመስገን ከወዳጅ ዘመዶቹ ጋር በዓሉን ያከብራል ብለዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከ83 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች በሃይማኖት፣ በዘርና በቋንቋ ሳይለያዩ በራሳቸው መገለጫዎች በአንድነት ይኖራሉ ያሉት አባ ገዳ ጎበና፤ እነኚህ ብዝሃ ማንነቶች በራሳቸው የባህል አልባሳት አጊጠው አንዱ በሌላው ብሔር በዓል በመገኘትና በማክበር አብሮነታቸውን ለማጠናከር ያግዛል ብለዋል።



አባ ገዳ ጎበና ሆላ



ሀዳ ሲንቄ ሳራ ዱቤ

ከዚህ ውስጥ የኢሬቻ በዓል አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም የሕዝቦች ወንድማማችነት እንዲጠናከር፣ አብሮነት እንዲጎለብትና ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ሲሉ ገልጸዋል።

ኢሬቻ ለሕዝቦች አብሮነት መጎልበት ዓይነተኛ ሚና ያለው በመሆኑ ባህላዊ ዕሴቶቹ ተጠብቀው ለትውልድ እንዲተላለፍ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት ብለዋል።


የሀዳ ሲንቄዎች ጉባኤ አባል ሳራ ዱቤ በበኩላቸው፤ ኢሬቻ የአንድ ሀገር ልጆች በአንድ ቦታ ተሰባስበው ሀገራዊ ዕሴታቸውን የሚያዳብሩበት የወንድማማችነት መገለጫ መሆኑን ገልጸዋል።

በኢሬቻ ዕለት ከተለያዩ የኦሮሚያ ዞኖች በተጨማሪ ከኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚሳተፉ የአንድ ሀገር ልጆች በአንድነት የሚሰባሰቡበት፤ በፍቅር የሚደምቁበትና የሚጠያየቁበት በዓል መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢሬቻ በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ተሳታፊዎች የሚታደሙት ከመሆኑም በላይ ሴቶች፣ ወንዶች፣ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች እና ሃዳ ሲንቄዎች በውብ አለባበስ ደምቀው የሚያከብሩት የውበት በዓል በመሆኑ ከፍተኛ የቱሪዝም ሀብት እንደሆነም አስረድተዋል።

ኢሬቻ በአባ ገዳዎች እና ሃዳ ሲንቄዎች አደይ አበባ እና እርጥብ ሳር በመያዝ «መሬሆ» በማለት ሲጫወቱ ወጣቶች ባህላዊ ጭፈራ እና ዘፈን የሚያሳዩበት ባህላዊ የጥበብ መድረክ ነው ያሉት ሀዳ ሲንቄ ሳራ፤ በዚህም ከሀገር ውስጥና ከውጭ በርካታ ቱሪስቶችን በመሳብ ለሀገር ኢኮኖሚ መነቃቃት ከፍተኛ ድርሻ ይጫወታል ብለዋል።

የኢሬቻ በዓል የቱሪዝም ምንጭ ሆኖ እንዲያገለግል ሥርዓቱን በጠበቀ መንገድ ማክበር ያስፈልጋል። የበዓሉ ዕሴት ሳይበረዝ እንዲቀጥል የበዓሉ ባለቤት የሆነው መላው ሕዝብ በፍቅር፣ በሰላምና በአንድነት እንዲያከብረው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።



# በአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር እየተገነባ የሚገኘው ሙዚየም የሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት አጋጠመው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በ1 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር እየተገነባ የሚገኘው የአማራ ሕዝብ ሙዚየም ግንባታ ሂደት ላይ ከፍተኛ የሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት መኖሩን የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ ዶክተር አየለ አናውጤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአማራ ክልል የሚገኙ ቅርሶችን ለማሰባሰብ በ1 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር እየተገነባ የሚገኘው የአማራ ሕዝብ ሙዚየም ግንባታ ሂደት ላይ ከፍተኛ የሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት አጋጥሟል፡፡

የአማራ ሕዝብ የበርካታ ታሪክ፣ ባህልና ቅርስ ያለው ሕዝብ ቢሆንም ይህንን በተደራጀ መንገድ ለአሁኑ ትውልድ ማስተማሪያ፣ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ብሎም ለጥናትና ምርምር በሚያስችል መልኩ የተደራጀ ሙዚየም አልነበረም፡፡

በመሆኑም ክልሉ ያሉትን ቅርሶችና ታሪኮችን ጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ የክልሉ መንግሥት በባህር ዳር ከተማ 15 ሺህ 600 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ሙዚየም ግንባታ እየተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ግንባታው በ2015 ዓ.ም የተጀመረ መሆኑን ጠቅሰው፤ በክልሉ ካለው የጸጥታ ችግር ባለፈ ለግንባታው የሚሆኑ የግብአቶች እጥረት አጋጥሟል ብለዋል፡፡

በተለይም ሙዚየሙ ግዙፍ ከመሆኑ ጋር ተያያዥ ከፍተኛ የሲሚንቶ ፍጆታ የሚፈልግ ቢሆንም የሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት ምክንያት ግንባታው በሚፈለገው ፍጥነት እየሄደ አለመሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ግንባታው የመሠረት ሥራው እየተገነባ ሲሆን፤ ያለው የግብአት መጓደል ተፈትቶ ግንባታው በፍጥነት እንዲቀጥል ለማድረግ ኮንትራክተሩ የተለያዩ አማራጮችን እንዲጠቀም አቅጣጫ አስቀምጠናል ብለዋል፡፡

ሙዚየሙ የክልሉ ማህበረሰብ አለባበስ ሥርዓትን ጨምሮ የሕዝቡን ማንነት በሚወክል መልኩ የታሪክ ክፍል፣ የባህልና የኪነጥበብ፣ የተፈጥሮ ሀብቶች፣ መዳረሻዎችንና ቅርሶችን በአጠቃላይ የአማራ ሕዝብ ባህልና ወግ በሚገልጽ መልኩ የተደራጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ግንባታው በራሱ እንደአንድ ህንጻ የሚገነባ ሳይሆን በክልሉ በዩኔስኮ ያስመዘገባቸውን ቅርሶች በሚወክል መልኩ ውጫዊና ውስጣዊ ዲዛይን የሚሠራ መሆኑን አስታውቀው፤ ኤግዚቢሽን እና ዘመናዊ አዳራሾችን ያካተተ መሆኑን ዶክተር አየለ ጠቅሰዋል፡፡

ይህ ወቅቱ የደረሰበት አጠቃላይ ሙዚየም ሲጠናቀቅም ግብአት የሚሆኑ ቅርሶችን በክልሉ ሁሉም አካባቢዎች የማሰባሰብ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ተንቀሳቃሽ ያልሆኑ ቅርሶችን በኪነጥበብ በሚወክል መልኩ የሚቀርብ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የሙዚየሙ መገንባት ለቅርሶች ጥበቃ ከማድረግ እና ለትውልድ ከማስተላለፍ ባለፈ ለጎብኚዎች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የቱሪዝሙን ዘርፍ በማዘመን በክልል ብሎም በሀገር ደረጃ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ዶክተር አየለ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም የዚህ ግዙፍ የአማራ ሕዝብ ሙዚየም ግንባታ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በመፍታት ግንባታውን ለማከናወን በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

# በመዲናዋ የተሠሩ መጸዳጃ ቤቶች በተያዘው ወር መጨረሻ አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ኮሪደር ልማትን ተከትለው የተገነቡት የመጸዳጃ ቤቶች በተያዘው የመስከረም ወር መጨረሻ አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምሩ የከተማዋ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የዘላቂ ማረፊያና የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ አጃይብ ኩምሳ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባስቀመጡት አቅጣጫ መሠረት በከተማዋ አምስቱም የኮሪደር ልማት አቅጣጫዎች የተሰሩ መጸዳጃ ቤቶች በተያዘው የመስከረም ወር መጨረሻ አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ፡፡

በከተማዋ በአጠቃላይ ወደ አንድ መቶ የሚደርሱ መጸዳጃ ቤቶች ሁሉንም መስፈርት እንዲያሟሉ ተደርገው በፅዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ የተገነቡ ሲሆን፤ አሁን ላይም አስፈላጊ መሠረተ ልማት የማሟላቱ ተግባር እየተጠናቀቀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

መጸዳጃ ቤቶቹ የወንድ፣ የሴት፣ የሕፃናት የዳይፐር መቀየሪያ እና የሴቶች የተፈጥሮ ንጽህና መጠበቂያና የእጅ መታጠቢያ ቦታዎችን ያሟሉ ብሎም ከመግቢያቸው ጀምሮ አካል ጉዳተኞችን ያማከሉ እንዲሆኑ በትኩረት የተሠሩ ምቹ እና ሁሉንም ያካተተ አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

አገልግሎቱን ለማግኘትም የትኬት መቁረጫ ቦታዎች በነባር የመጸዳጃ ቤቶች ክፍያ ተመን መሠረት እስከ 4 ብር ከፍሎ መገልገል የሚቻል መሆኑን አቶ አጃይብ ተናግረዋል፡፡

የተገነቡት መጸዳጃ ቤቶች ከተማውን ጽዱ የማድረግ ዓላማ በመያዝ ከዚህ በፊት ባልነበረ ሁኔታ የከተማውን ደረጃ፣ ውበት እና የነዋሪውን ክብር ጠብቀው የተገነቡ መሆናቸው የከተማው ለውጥ ነው ማለት ይቻላል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ይህ የከተማዋን ገጽታ የሚለውጥ መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ ሂደት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፤ በዚህ ዓመት የኮሪደር ልማቱን ጨምሮ ቢያንስ 200 መጸዳጃ ቤቶች ለመገንባት የታቀደ መሆኑን አቶ አጃይብ አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም መጸዳጃ ቤቶች መገንባት የማይቻልባቸው እንደ መገናኛ፣ መርካቶ፣ ሳሪስ፣ አየር ጤና እና ሽሮሜዳ ያሉ ጠባብና ግርግር የሚበዛባቸው ቦታዎች ላይ 60 ተንቀሳቃሽ መጸዳጃ ቤቶች ለመሥራት የታሰበ መሆኑን ጠቅሰው፤ እስካሁን ባለው ሂደትም 40 የሚሆኑ ተንቀሳቃሽ መጸዳጃ ቤቶች ግዢ የተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች የአካባቢን ንፅህና ከመጠበቅ ባለፈ ከተማዋ ካላት ተጽእኖ አንጻር እስካሁን የተገነቡትና ወደፊት የሚገነቡት መጸዳጃ ቤቶች ምቹ እና ለከተማው ውበት ሆነው ሁሉንም የሚመጥን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ናቸው ብለዋል፡፡

በመሆኑም የተገነቡ መጸዳጃ ቤቶች የከተማዋ አንዱ የውበት መገለጫዎች ስለሆኑ ሁሉም አገልግሎቱን በባለቤትነትና በኃላፊነት መገልገል እንደሚገባ አቶ አጃይብ አሳስበዋል፡፡

# የአፍሪካ ውክልና - በጸጥታው ምክር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ቢሊዮን በላይ ሕዝብ ለአላት የአፍሪካ አህጉር በምክር ቤቱ ቋሚ ድምጽ አለመኖር ተቀባይነት የሌለው መሆኑም የብዙኃኑ አስተያየት ነው።

ኢትዮጵያም በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ በኩል ሰኞ ዕለት መስከረም 13 ቀን 2017 በኒውዮርክ በተካሄደው 79ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የተ.መ.ድ የፀጥታው ምክር ቤት ማሻሻያ የአፍሪካን እውነተኛ ውክልና ባረጋገጠ መልኩ እንዲከናወን ጠይቃለች።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ጥያቄያቸውን ባቀረቡበት ወቅት ምክር ቤቱን ለማሻሻል የሚደረገው እንቅስቃሴ የአፍሪካን የውክልና አድማስ ከሁሉም መመዘኛዎች አንጻር ታሳቢ ሊያደርግ እንደሚገባው ጠይቀዋል።

አፍሪካ በጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ ብታገኝ በተለይ ጦርነትና አለመረጋጋቶችን በቀጣናው ከመቀነስ በተጨማሪ ውሳኔ ሰጪነትን ከማሳደግና አህጉራዊ ጥቅሞችን ከማስጠበቅ ረገድ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት መምህር እና የሕግ አማካሪ ተስፋዬ አባተ (ዶ/ር) ለኢፕድ በሰጡት ቃል አህጉሪቱ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ ውክልና የሚሰጣት ከሆነ በተለያዩ ዘርፎች ያላትን ፍላጎት ተግባራዊ እንድታደርግ ያግዛታል ይላሉ።

አፍሪካ እንደ አህጉር ጥቅሞቿን ለማስከበር፣ አጀንዳዎቿን ለማስጠበቅ እና ተሰሚነቷን ለማሳደግ የሚኖረው አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ባይ ናቸው።

አፍሪካ እንደ አፍሪካ እስከ አሁን በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ ባለማግኘቷ ለከፍተኛ ጉዳት ዳርጓታል የሚሉት ዶክተር ተስፋዬ፤ በተለይ አፍሪካ በሌለችበት የሚሰጠው ውሳኔ የአህጉሪቱን ነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም ሙሉ ጠባይዋን ያላገናዘበ ውሳኔ እንደሚሆን ይጠቁማሉ።

ዶክተር ተስፋዬ እንደሚገልጹት፤ ታዳጊ ሀገራት የራሳቸው የማደግ ፍላጎት ያላቸው በመሆኑ የማደግ ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። ነገር ግን እስካሁን ባለመሆኑ ግን እድገቱ እንዲቀጭጭ ማድረጉንም ያብራራሉ።

አፍሪካ በድርጅቱ ቋሚ መቀመጫ የምታገኝ ከሆነ ድምጽን በድምጽ የመሻር ዕድልን ለመጠቀም የሚረዳት መሆኑንም ያስረዳሉ።

አፍሪካ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ እንድታገኝ ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ተጋድሎ ማድረግ ያስፈልጋል የሚሉት ዶክተር ተስፋዬ፤ ከዚህ ቀጥሎም በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ አፍሪካ እንደ አህጉር የመልማት አቅም የማሳየትና የመሪነት ሚና ማሳደግ ይጠበቅባታል።

ከዲፕሎማሲው ጎን ለጎንም ባለሙያዎች በየመስኩ ሙያቸውን በተገቢው መንገድ ማከናወን እንዲሁም በቴክኖሎጂ ረገድ ዓለም እያደረገች ያለችውን የቴክኖሎጂ ለውጥ መከተልና መተግበርም ለዚህ የሚረዳ እንደሆነ ያክላሉ።

በአንጎላ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ፣ የመካካለኛው ምሥራቅና የቀጣናዊ ጉዳዮች ዳይሬክተር አምባሳደር ጆርጅ ካታሪና እንደሚሉት፤ አፍሪካ ከ70 ዓመታት በላይ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ ሳታገኝና ፍላጎቷን ሳታሳካ ቀርታለች።

የአፍሪካ ሰላምና ደህንነት ችግሮች በተመለከተ በጸጥታው ምክር ቤት አፍሪካ ባልተገኘችበትና ድምጿን ባልሰጠችበት ሁኔታ ተፈጻሚ እየሆነ መቆየቱንም ይጠቁማሉ።

በተለይ አሁን ላይ የዓለም ሕዝቦች የአሰፋፈርና አስተዳደራዊ መዋቅር ጋር ተያይዞ አካታችና ሁሉን አቀፍ ውሳኔ ለመስጠት የተ.መ.ድ.ጸ.ም.ት ሪፎርም የሚያስፈልገው ስለመሆኑንም ያብራራሉ። ይህም አስፈላጊነቱ ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው ታዳጊ ሀገራትም ጭምር ነውም ይላሉ።

በተ.መ.ድ የዩናይትድ ኔሽን አምባሳደር ሊንዳ ቶማስ-ግሪንፊልድ በበኩላቸው ዓለም ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የጸጥታው ምክር ቤት ተገቢውን ሪፎርም ማድረግ ያስፈልገዋል ባይ ናቸው።

አሁን ላይ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ውስብስብ ችግር ተጋርጦበታል የሚሉት አምባሳደር ቶማስ-ግሪንፊልድ፤ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ጦርነት እንዲሁም ኮቪድ-19 በዋናነት ተጠቃሽ መሆናቸውን ያስታውሳሉ።

አሁን በዓለም ላይ እያጋጠሙ ያሉት የተለያዩ ችግሮች አካታች የጸጥታ ምክር ቤት አለመኖሩ ማሳያ ነውም ይላሉ።

አሜሪካ ለአፍሪካ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ላይ ሁለት ቋሚ መቀመጫ እንዲኖራት ድጋፍ እንደምታደርግ ጠቅሰው፤ ምክር ቤቱ ውይይት ብቻ ማድረግ ሳይሆን ወደ ተግባር መግባት እንዳለበትም ይመክራሉ።

# ከጉባኤው ጎን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሶማሊያን በተመለከተ የቀጣናው ሀገራት ዋጋ የከፈሉበት እና የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከፍተኛ ወጪ የወጣበት የሶማሊያ ደህንነት እንዲቀጥል ማድረግ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል። ከድህረ አትሚስ በኋላ የሚኖረው የኃይል ሥምሪት ጊዜ ተወስዶ በጥንቃቄ መከናወን እንዳለበት ገልጸዋል።

ከሕንድ አቻቸው ዶክተር ሱብራማንያ ጄይሻንካር ጋር ባደረጉት ውይይትም፤ ሁለቱ ሚኒስትሮች የጋራ ፍላጎት በሚሹ ሁለትዮሽ እና ባለብዙ ወገን ግንኙነት ዙሪያ መክረዋል።

ከግሪኩ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጊኦርጎስ ጀርፐትራይተስ ጋር ባደረጉት ውይይትም፤ ግሪክ የተመድ የጸጥታው ምክር ቤት አባል ሆና በመመረጧ የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል። ኢትዮጵያ የምታደርገውን ፀረ-ሽብር ዘመቻ አጠናክራ ለመቀጠል ያላትን ቁርጠኝነት ገልጸዋል።

አምባሳደር ታዬ ከሴራሊዮን ውጭ ጉዳይ እና ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስትር ጢሞቲ ካባ ጋር በአፍሪካ ቀንድ ሰላም እና ደኅንነት ዙሪያ መክረዋል።

አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ከተመድ የሰላም ኦፐሬሽን ረዳት ዋና ፀሐፊ ዣን ፒዬር ለክሮይ ጋር ባደረጉት ውይይት ረዳት ዋና ፀሐፊው ኢትዮጵያ ለተመድ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ያላትን አስተዋፅኦ እና ከድርጅቱ የሰላም ኦፐሬሽን ጋር የፈጠረችውን ጠንካራ ግንኙነት አድንቀዋል።

አምባሳደር ታዬ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ሽብርተኝነትን በመዋጋት ያላትን ቁርጠኝነት ገልጸው፤ በሶማሊያ ከድህረ አትሚስ በኋላ የሚኖረው የኃይል ስምሪት በቂ ጊዜ ተወስዶ በጥንቃቄ መከናወን እንዳለበት አሳስበዋል።

አምባሳደር ታዬ፤ ከሩዋንዳ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ኦሊቨር ኒዱሁንጊሬሄ እና ከኡጋንዳ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጄጄ ኦዶንጎ ጋር በተናጠል ተወያይተዋል።

አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ከሩዋንዳው አቻቸው አምባሳደር ኦሊቨር ኒዱሁንጊሬሄ ጋር በነበራቸው ውይይት የናይልን ወንዝ የውሃ ሀብት ፍትሐዊ እና እኩል ለመጠቀም ለትብብር ማዕቀፉ ስምምነት ትግበራ በጋራ ለመሥራትም ተስማምተዋል።

ኢትዮጵያ እና ኡጋንዳ ለሶማሊያ ሰላም ማስከበር ወታደር ካዋጡ ሌሎች ሀገራት ጋር በመሆን ከድህረ አትሚስ በኋላ የሚደረግ ማንኛውም ችኮላ የተሞላበት ስምምነት ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ እስካሁን የተገኙ ስኬቶችን አደጋ ላይ ይጥላል የሚል የጋራ ስጋት እንዳላቸው ገልጸዋል።

የትብብር ማዕቀፍ ስምምነቱ ወደ ተግባር መቀየሩ የጋራ ሀብትን ፍትሐዊ እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀም እና በተፋሰሱ ሀገራት መካከል ያለውን ትብብር ከፍ ለማድረግ አወንታዊ እድገት መሆኑን አምባሳደር ታዬ ጨምረው ገልጸዋል።

ከአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳይ ረዳት ሚኒስትር ሞሊ ፊ ጋር በነበራቸው ቆይታም፤ አሜሪካ ሽብርተኝነትን በመዋጋት እና አጠቃላይ በቀጣናው ሰላም እና መረጋጋት ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ትብብር አጠናክራ እንደምትቀጥል አረጋግጠዋል።

ከቻይናው አቻቸው ዋንግ ዪ ጋር ባደረጉት ውይይትም ሚኒስትሩ የሁለትዮሽ ግንኙነታቸው "የምንጊዜም ስትራቴጂክ አጋርነት" (All Weather Stratagic Partnetship) መሆኑ በቀጣይ በርካታ ሥራዎችን በጋራ ለመሥራት መሠረት የጣለ መሆኑን ገልጸዋል።

በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የቻይና ጉብኝት ወቅት ስምምነት የተደረሰባቸው የኢኮኖሚ ትብብር ፕሮጀክቶች እንዲሁም ከቀረጥና ታሪፍ ነፃ የገበያ ዕድሎች ትኩረት ተሠጥቷቸው ተግባራዊ እንደሚደረጉ አስታውቀዋል።

ከ.ተ.መ.ድ. የሰላም ግንባታ እና ፖለቲካ ጉዳዮች ረዳት ዋና ፀሐፊ ሮዝማሪ ዲካርሎ ጋር ባደረጉት ውይይትም፤ በሱዳን ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የተቀናጀ ጥረት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል። ኢትዮጵያ ለሱዳን ቀውስ መፍትሔው ፖለቲካዊ ነው የሚል አቋም እንዳላት አንስተዋል።

አምባሳደር ታዬ ሶማሊያን በተመለከተ ከሮዝማሪ ጋር በነበራቸው ውይይት ኢትዮጵያ ሽብርተኞችን ለመዋጋት የምታደርገውን ጥረት አጠናክራ እንደምትቀጥል አረጋግጠዋል።

ከአልጄሪያ አቻቸው ጋር ባደረጉት ውይይት ኢትዮጵያና አልጄሪያ በአፍሪካ አህጉር በሚታዩ የሰላምና ፀጥታ ጉዳዮች ይበልጥ ተቀናጅተው ሊንቀሳቀሱ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ሚኒስትሮቹ በቅርቡ ለሚካሄደው አምስተኛው ኢትዮ - አልጄሪያ የጋራ ኮሚሽን ስብሰባ ሃሳብ ተለዋውጠዋል።

የ.ተ.መ.ድ 79ኛ ጠቅላላ ጉባዔ "ማንንም ወደ ኋላ አለማስቀረት፤ ለአሁኑ እና ለመጪው ትውልድ ሰላም፣ ዘላቂ ልማት እና ሰብአዊ ክብር በጋራ መሥራት" በሚል መሪ ሃሳብ ከመስከረም 14 እስከ 20 ቀን 2016 ዓ.ም በኒውዮርክ በመካሄድ ላይ መሆኑ ይታወቃል።

# መንፈስንም ጉልበትንም አዳሹ ልማት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ስጋቸው ደግሞ ለሰው ምግብነት የሚሆን ነው።

ይህ በሸገር ከተማ አስተዳደር፣ በኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ፣ በገላን አራብሳ ወረዳ ነዋሪ የሆነው ወጣት መስፍን፣ የዲፕሎማ ምሩቅ ነው። ይሁንና ተቀጥሮ መሥራትን አልመረጠም። በቤተሰብ ደረጃ በመደራጀት መንግሥት ባመቻቸላቸው መሠረት ወደዓሳና ንብ እርባታ መግባታቸውን ያስረዳል። በሁለቱ ሥራ ብቻ ሳይወሰኑ ሰንጋ በማደለብና በመስኖ ስንዴን በማልማት ላይም እንደሚገኙ ይገልጻል።

ወጣቱ አርሶ አደር፣ ብዙ ርቀ መሄድ ሳይጠበቅበት በቀዬው ሆኖ በደጃፉ የሚያስፈልገውን የገላንን ወንዝ በሞተር ታግዞ በመጥለፍ የቆፈሯቸውን ሁለት ጉድጓዶች ውሃ በመሙላት ወደ ዓሳ እርባታው በ2016 ዓ.ም መግባታቸውን ያስረዳል። በወቅቱም 400 ያህል የዓሳ ጫጩቶችንም ከሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል በወረዳቸው አማካይነት ማግኘታቸውን ያመለክታል።

"በእርግጥ በዓሳ ምርት ውጤት ይገኛል የሚል ሃሳብ አልነበረኝም ነበር። ነገር ግን በመስከረም የተጀመረው የዓሳ እርባታ ከስድስት ወር በኋላ ወደ 300 ያህል ዓሳ ለገበያ ማቅረብ አስችሎናል። ከአራት ወር በኋላ ደግሞ እንደ ሸገር ከተማ ክፍለ ከተማ በባዛር የዓሳ ምርት ይዘን ቀርበናል።" ይላል።

እርሱ እንደሚለው፤ ከዓመት በፊት ወደ ውሃው ኩሬ የገቡት 400 የዓሳ ጫጩቶች፤ ዛሬ በብዙ እየተሸጡም በእጥፍ ጨምረዋል። ስጋት የሆነን ግን የጉድጓዱ መጥበብ ነው። ከዚህ የተነሳ ከአንድ ወደ ሁለት፤ ከሁለት ደግሞ ወደሶስት የውሃ ጉድጓድ በመሸጋገር ላይ ይገኛሉ። በአንደኛው ጉድጓድ ወደ ሦስት ሺህ 500 ያህል ዓሳ፣ በሁለተኛው ጉድጓድ ደግሞ ወደ አምስት ሺህ ዓሳዎች ይገኛሉ። ሦስተኛው ጉድጓድም በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

ዓሳ፣ ከዚህ ቀደም በሌማታችን ውስጥ እምብዛም የማይካተት ነው፤ ዛሬ ግን ዋነኛ ምግብ ከመሆኑም በተጨማሪ ለሽያጭ በመጠቀም ውጤት እያገኘንበት ነው።

ይህን ያስተዋሉ የአካባቢው አርሶ አደሮችም ሆኑ ወጣቱ ወደግቢያቸው ጎራ እንደሚሉ ጠቅሶ፤ ዓሳ ማምረት እንደሚፈልጉና ተሞክሮውንም እንደሚቀስሙ ይገልጻል።

መስፍን እንደሚናገረው፤ ከዓሳ እርባታ በተጨማሪ ማርም በማምረት ላይ ናቸው፤ በዓመት ሁለቴ ይቆርጣሉ። ቀደም ሲል ከአንድ ባህላዊ ቀፎ የሚገኘው ግፋ ቢል ሁለትና ሦስት ኪሎ ቢበዛ ደግሞ አምስት ኪሎ ማር ነው። ከዘመናዊው ቀፎ ግን እስከ 20 ኪሎ መቁረጥ ይችላሉ። እስከ 40 ያህል ባህላዊ የንብ ቀፎ ቢኖረውም ውጤቱ ያን ያህል ነው። በአሁኑ ወቅት 45 ያህል ዘመናዊ ቀፎ አላቸው። ይህን በእጥፍ የማሳደግ እቅድም ይዘዋል።

ወጣቱ አርሶ አደር፣ በበጋ ወቅት የገላን ወንዝ የተፈለገውን ያህል ውሃ ሊሰጥ ስለማይችል የውሃ ችግር ስጋት እንደያዛቸው አስረድቷል። የዓሳ ምርቱንም ለማውጣት የሚያስችል መረብም ችግር እንደሆነባቸው ተናግሯል።

የገላን አራብሳ ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አዲሱ በበኩላቸው፤ እንደ ገላን አራብሳ ወረዳ ያለው ኢኒሼቲቭ መልካም የሚባለው ነው ይላሉ። በተለይም የዓሳና የንብ ልማትን በተመለከተ ውጤታማ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል። የክልሉ መንግሥት ባስቀመጠው ኢኒሼቲቭ መሰረት አርሶ አደሮች እንደየፍላጎታቸው በቤተሰብ ደረጃ ተደራጅተው ወደሥራ መግባታቸውን አስታውሰው፤ ጾሙን ያድር የነበረው መሬት ሁሉ አገልግሎት መስጠት መጀመሩን ጠቅሰዋል።

ኃላፊው እንደሚሉት፤ አርሶ አደሩ ወደሥራ ከመሰማራቱ በፊት የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ሰፊ ግንዛቤ እንዲፈጠርለት ተደርጓል። ከዚህ የሥራ መስክ ውስጥ እንደወረዳው የዓሳና የማር ልማት ተጠቃሽ ሲሆን፤ በተለይም በዓሳ ምርት የወጣቱ ተሞክሮ ሌሎቹም ወጣቶችና አርሶ አደሮች እንዲያገኙ በማድረግ ወደሥራው እንዲገቡ በማበረታታት ላይ ይገኛሉ።

በሌላ በኩል ከማር ልማት ጋር በተያያዘ አርሶ አደሮቹ ባህላዊም ዘመናዊም የንብ ቀፎ አላቸው። ቀደም ሲል ያለው ባህላዊ ቀፎ ምንም አይነት ድጋፍ ሳይደረግለት የቆየ ነው። በአሁኑ ወቅት ባህላዊ የንብ ቀፎውንም ሙሉ ለሙሉ ሳያስወግዱ ወደዘመናዊ ቀፎ እንዲመጡ እያደረግን እንገኛለን። በተለይም በዘመናዊ ቀፎ እንዴት መስራት እንደሚቻል በቤተሰብ ደረጃ አደራጅተን አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ አድርገናል። ቀስ በቀስም በእንዲህ አይነት ሁኔታ ወደ ዘመናዊ ቀፎ እንዲሸጋገሩ እንፈልጋለን ብለዋል።

የገበያ ችግር አለመኖሩን የጠቀሱት አቶ አዲሱ፤ በባዛር ላይ ዓሳ እና ማር በማቅረብ ላይም እንደሚገኙ ተናግረዋል። እንደወረዳችን በማር ኢንሼቲቭ ላይ የተለያዩ አርሶ አደር ቤተሰቦች በማር ልማት እንዲደራጁ ተደርገው እየሠሩ ይገኛሉ። በዚህም ወደ 14 ያህል ማህበር መሰማራታቸውን አመልክተዋል።

የመረብ ችግር የተባለው አግባብነት ያለው ጥያቄ መሆኑን ጠቁመው፤ ብዙዎቹ አርሶ አደሮች ለተሞክሮ ወደወጣቱ አርሶ አደር ስለሚመጡ በዚህም የተሟላ ነገር ማየት አለባቸው ብለዋል። የዓሳዎችን ደረጃና አይነትም ለማሳየት ደግሞ ሁነኛ የሆነ መረብ አስፈላጊ እንደሆነ የሚታወቅ ነው። ይሁንና በአሁኑ ወቅት ባቱ አካባቢ ካሉ ዓሳ አምራች ማህበራት ጋር በመነጋገር ችግሩን ለመፍታት ከጫፍ ደርሰናል ሲሉ አስረድተዋል።

የውሃ ችግርን በተመለከተ የወንዙ ሁኔታ አሳሳቢ ቢሆንም፤ ወረዳችን ጥሩ የሆነ የከርሰ ምድር ውሃ አቅም ያለው እንደመሆኑ በዚህ ስጋት አይኖርም ብለዋል፤ ከዚህ ባለፈ ለበጋ መስኖ ልማት የሚሆን በቂ የሆነ ውሃ በመኖሩ ትንሽ ብቻ ቆፈር በማድረግ የጉድጓድ ውሃ በማውጣት ስንዴንም ማልማት የሚቻል ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ እንደ ወረዳችንም የተጀመረ ሥራ አለ። ስለዚህ ይህንኑ ሥራ እናሰፋለን ሲሉ መልሰዋል።

በሸገር ከተማ አስተዳደር ኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ የኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ የግብርና ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ ዶክተር ናፍያድ ዓለሙ እንደሚገልጹት፤ በከተማችን ሰፋፊ ሥራዎች በመሠራት ላይ ይገኛሉ። እነዚህም ሥራዎች ውጤታማ መሆን የቻሉ ናቸው። ውጤታማ ከሆኑት ሥራዎች አንዱ የሌማት ትሩፋት ሲሆን፤ አርሶ አደሩ በአግባቡ እየሠራበት ይገኛል።

እንደሚታወቀው በከተማ አስተዳደር ውስጥ የነበሩ አርሶ አደሮች በተለይም ደግሞ በኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ የነበሩ አርሶ አደሮች ከስፍራቸው በመፈናቀላቸው ሥነ ልቦናቸው የተጎዳ ነው። ስለዚህም ሥነ ልቦናቸው ከጉዳት እንዲወጣ በተለያዩ ቦታዎች ስልጠና ሰጥተናል። ስለዚህ ውጤት ማምጣት ተችሏል።

በአሁኑ ወቅት በየወረዳዎቹ ውጤታማ ልማት እየተካሔደ ሲሆን፤ በገላን አራብሳ የማር ልማትና የዓሳ ልማት አንዱ ተጠቃሽ ነው። በወረዳው ባለፈው ዓመት አመርቂ ሥራ ተሰርቶ ውጤት ተገኝቶበታል። የገበያ ሁኔታም ተመቻችቶላቸዋል ብለዋል። የዓሳ ልማቱን በተመለከተ ችግሩ በመረብ ብቻ ሳይሆን በቀፎ በኩልም እጥረት አለ። አስፈላጊ የሆኑ ግብዓት በሙላት ለማዳረስ እየተሠራ ነው። ለአርሶ አደሩ ተጨማሪ ስልጠናዎችንም የምንሰጥ ይሆናል። የዓሳም ሆነ የንብ ውጤትን ማስመዝገብ የሚቻለው በሂደት ነው ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሶማሊያ መንግሥት የጥፋት እንቅስቃሴ ለሀገሪቱ ችግር “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” ነው!

ከሽብርተኝነት እና ጽንፈኝነት ብዙ ዋጋ እያስከፈላቸው ከሚገኙ የዓለም ሕዝቦች በዋነኛነት ተጠቃሽ የሶማሊያ ሕዝብ ነው። የሕዝቡን ችግር ለመታደግ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ርምጃዎች ቢወሰዱም ለዘለቄታው ችግሩን መፍታት አልተቻለም። ችግሩ ከሶማሊያ ውጪ ለአካባቢው ሀገራትም ስጋት ከሆነ ውሎ አድሯል።

በሀገሪቱ የተከሰተውን መንግሥት አልባነት ተከትሎ አልሸባብን ጨምሮ ሌሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ ጽንፈኛ የሽብር ቡድኖች በሀገሪቱ በስፋት በመንቀሳቀስ የሀገሪቱን ማዕከላዊ መንግሥት እስከ መቆጣጠር የደረሰ አቅም ገንብተው እንደነበር፤በዚህም የሶማሊያ ሕዝብ ለብዙ መከራ እና ስቃይ መዳረጉ የሚታወስ ነው ።

ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በተመድ ፣ በአፍሪካ ኅብረት እና በኢጋድ በኩል የሰላም አስከባሪዎችን በመላክ ሕዝቡን ከሽብርተኛ እና ጽንፈኛ ኃይሎች ለመታደግ ረጅም ርቀት ተጉዟል። ከብዙ መስዋዕትነት በኋላም በሶማሊያ ማእከላዊ መንግሥት ከማቋቋም ጀምሮ መንግሥቱ በእግሩ እንዲቆም ሰፊ ጥረቶች ተደርገዋል።

ይህንን ዓለም አቀፋዊ ጥረት በግንባር ቀደምትነት በመደገፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት የአንበሳውን ድርሻ በመውሰድ ተንቀሳቀሰዋል። ኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይሏን በሶማሊያ በማሰማራት አልሸባብን ጨምሮ በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ አሸባሪ ቡድኖች በማዳከም የሀገሪቱ ሕዝብ አንጻራዊ ሰላም እንዲያገኙ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አበርክታለች።

ብዙ መስዋዕትነትን በጠየቀው በዚህ የሶማሊያ ሕዝብን ከአሸባሪዎች የመታደግ እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ብዙ መስዋእትነት በመክፈል ለሶማሊያ ሕዝብ ያለውን አጋርነት በተጨባጭ አሳይቷል። የአሸባሪዎችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በማምከን የሶማሊያ ሕዝብ ህይወቱን አንጻራዊ በሆነ ሰላም ውስጥ እንዲመራ አስችሏል።

ይህ በሁለቱ ሀገራት ሕዝቦች የወንድማማችነት ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት በህይወት መስዋእትነት የጻፈው ታሪክ ፣ በሶማሊያውን ዘንድ ትልቅ ከበሬታ የተሰጠውና አሁን እንደሀገር ላሉበት አንጻራዊ ሰላም እና በቀጣይ እንደሀገር ለሚኖራቸው ቁመና መሰረት የጣለ ነው።

የሶማሊያ ሕዝብ ካሳለፋቸው አስቸጋሪ ትናንቶች አኳያ አሁን ላይ በብዙ መስዋእትነት ያገኘውን ሰላም ጠብቆ ከማስቀጠል ባለፈ፤ ድንበር ተሻግረው የሚመጡ አጀንዳችን ተቀብሎ በገዛ ሰላሙ ላይ በተቃርኖ የሚቆምበት ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖረውም። ሰላም አልባ ሆኖ ከከፈለው ዋጋ አንጻር ሰላም እና ለሰላም የሚከፈል ዋጋ የቱን ያህል ውድ እንደሆነ ይረዳልና።

የመሪዎች ያልተገባ እብሪት እና የውጪ ኃይሎች ሆይ ሆይታ ምን ያህል ሀገር እንደ ሀገር እንደሚያፈርስ፤ ሀገርን ሕግ እና ሥርዓት አልባ አድርጎ ዜጎችን ለከፋ ስቃይ እና መከራ እንደሚዳርግ እስከ ዛሬ ሀገራዊ ፈተና ከሆነባቸው የትናንት ታሪካቸው በተጨባጭ መረዳት እንደሚችሉም መገመት የሚከብድ አይደለም ።

የሶማሊያ ሕዝብ አሁናዊ መሻቱ ከትናንት የመሪዎቹ ስህተት ተምሮ፤ለሰላሙ እና ብሔራዊ ደህንነቱ ዘብ መቆም ነው። ይህ ደግሞ ከሁሉም በፊት ለሰላሙ እና ለብሄራዊ ደህንነቱ ስጋት የሆኑ የሽብር ኃይሎች መቋቋም የሚያስችል ሀገራዊ አቅም መገንባት ነው። ዜጎችን ለዚህ ብሔራዊ ተልዕኮ በአንድነት ማሳለፍ የሚያስችል አጀንዳ ፈጥሮ መንቀሳቀስ ነው።

የሀገሪቱን ሰላም እና ብሔራዊ ደህንነት ለማስከበር ከፍ ባለ የወንድማማችነት መንፈስ በሀገሪቱ እየተንቀሳቀሱ ከሚገኙ አፍሪካውያን የሰላም አስከባሪ ኃይሎች ጋር ተቀናጅቶ በመሥራት፤ የሽብር ቡድኑ ለሀገሪቱ ስጋት የማይሆኑበት ተጨባጭ ሀገራዊ እውነታ መፍጠር ነው።

ከዚህ ውጪ የሀገሪቱ መንግሥት አካባቢን የግጭት እና ያለመረጋጋት ማዕከል ለማድረግ ከሚንቀሳቀሱ የውጪ ኃይሎች የጥፋት እንቅስቃሴ ጋር ኅብረት አድርጎ ለመንቀሳቀስ የሚደረገው ጥረት ከሁሉም በላይ የሶማሊያን ሕዝብ ለከፋ መከራ እና ስቃይ የሚዳርግ እና ፤የሀገሪቱን ብሔራዊ አንድነት አደጋ ውስጥ የሚከት ነው።

የሶማሊያ መንግሥት እየሄደበት ያለው የጥፋት መንገድ እንደ መንግሥት ከትናንት ስህተት ለመማር ፈቃደኝነት ከማጣት የመነጨ፣የውጪ ኃይሎችን አጀንዳ ተቀብሎ በሀገር ዕጣ ፈንታ ላይ የመጫን ፣ራስን በራስ የማጥፋት ሙከራ ተደርጎ የሚወሰድም ነው፤ ፍጻሜውም የሽንፈት ታሪክን ከመድገም ባለፈ ፋይዳ አይኖረውም።

በተለይም አሁን ላይ አካባቢውን የግጭት ቀጣና ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ ታሪካዊ ኢትዮጵያ ጠላቶች ወደ ሶማሊያ እያጓጓዙት ያለው የጦር መሳሪያ ፤ ራሱን በአግባቡ መከላከል ከማይችለው የመንግሥት ኃይል እጅ ወጥቶ አሸባሪ ቡድኖች እጅ ከገባ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ለሶማሊያ ሕዝብ “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” መሆኑ የማይቀር ነው!

አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## «የግብጽ አካሄድ፤ በጥባጩ ካለ ጥሩ አይጠጣምና...»

ስሜነህ ደስታ

በገጠር አካባቢ ውሃ ከምንጭ ሲቀዳ ከአቆተው ቀስ ብሎ በጣሳ ወይም በቅል ተደርጎ ወደ እንሥራ ነው የሚገለበጠው እንጂ፣ እጅ እንዳመጣ ወደ አቆተው ውሃ አይጠለቅም፡፡ ምክንያቱም ውሃው ስለሚበጠበጥ ይደፈርሳል፡፡ ይህን ሥርዓት ተከትለው አብዛኞቹ የገጠር እናቶች የሚበቃቸውን ያህል ይቀዳሉ፤ ቀጣይ ለምትቀዳውም በማሰብ እንዳይደፈርስ ይጠነቀቃሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ግን ከአቆተው ለራሳቸው ቀስ ብለው ቀድተው ከጨረሱ በኋላ ለቀጣይ ሰው ባለማሰብ የጠለለውን ውሃ የሚያደፈርሱ አሉ፡፡ ‹‹እኔ ከበላሁ ሰርዶ አይብቀል›› እንዳለችው አህያ ዓይነት መሆኑ ነው፡፡ ለሌላው መብትና ጤና ሳያስቡ ውሃውን በጥብጠውት ይሄዳሉ፡፡ እንዲህ የሚያደርጉት አብዛኛውን ጊዜ ሰው ሳያያቸው ነው፡፡ በእርግጥ ሰው እያያቸውም ቢሆን፣ ተረኛ አጠገባቸው እየተጠባበቃቸውም ቢሆንም ግድ የሌላቸውም አሉ፡፡ ዋናው ዓላማቸው ማደፍረስ ሌላው ንፁህ እንዳይጠጣ ማድረግ ነው፡፡

እንዲህ አድርገው የሚያደፈርሱ ሲገኙ፣ ሌሎች ውሃ ቀጂዎች በቅድሚያ እንዴት ተደርጎ እንደሚቀዳ ከማሳየትና ከመምከር በመጀመር፤ አልስተካከልም የሚሉትን በህብረት ሆነው እስከመጣላት ይደርሳሉ፡፡ በዚህ አግባብ የማይስተካከሉትን ደግሞ ማህበረሰቡ ውሃው አጠገብ እንዳይደርሱ ያግዳቸዋል፤ ይከታተላቸዋል፤ በጥባጭ ካለ ጥሩ ስለማይጠጣ፡፡

> ግብጽም «እኔ ከበላሁ ሰርዶ አይብቀል»እንዳለችው አህያ ሆና፣ ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ኢትዮጵያ ጥሩ እንዳትጠጣ ታደፈርሳለች፣ ትበጠብጣለች፡፡ የህዳሴ ግድቡ ሲገነባ ማንኛውም አካል ምንም እንከን እንዳያጋጥመው በማሰብ ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ጥረት አድርጋለች

ግብጽም ‹‹እኔ ከበላሁ ሰርዶ አይብቀል›› እንዳለችው አህያ ሆና፣ ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ኢትዮጵያ ጥሩ እንዳትጠጣ ታደፈርሳለች፣ ትበጠብጣለች፡፡ የህዳሴ ግድቡ ሲገነባ ማንኛውም አካል ምንም እንከን እንዳያጋጥመው በማሰብ ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ጥረት አድርጋለች፡፡

በተለይ ኢትዮጵያ ከግብጽና ከሱዳን ጋር የሦስትዮሽ ውይይት ለማድረግ በሙሉ ልብ ተንቀሳቅሳለች፡፡ ይሁንና ግብጽ ሱዳንን በማስተባበር ውይይቱ መስመር እንዳይዝ ብሎም ግድቡ እንዳይገነባ የተለያዩ እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ ሃሳቦችን ስትደረድር ቆይታ በስተመጨረሻ ውይይቱን አቋርጣ ወጥታለች፡፡

ኢትዮጵያ ግን አሁንም ቢሆን ሁሉን ሊያግባባ የሚችል ሥምምነት ላይ ለመድረስ ያላትን ቁርጠኝነት እያሳየች ነው፡፡ በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር ወይም በአጠቃላይ የትብብር ሕግ ማዕቀፍ ስር የሦስትዮሽ ድርድሩን ለመቀጠልና የሁሉንም ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ስምምነት ላይ ለመድረስ ቁርጠኝነት አላት፡፡

ግብጽ ግን ድርድሩ ውስጥ የምትገባው በሙሉ ልብ ሳይሆን የውስጥ ችግር ሲያጋጥማት ወይም የአጋሮቿን ድጋፍ ላለማጣት ለይስሙላ ነው፡፡ ጉንጭ አልፋ ውይይት በሚደረግባቸው ባለፉት ዓመታት ውስጥ ግድቡ እንዳይገነባ ያልሸረበችው ሴራ፣ ተባባሪ ሆነው እንዲያግዟት ያልተማፀነችው አካል የለም፡፡ አሁን የታላቁ ህዳሴ ግድብ የግንባታ ሥራው ተጠናቆ በከፊል ሥራ በመጀመሩ በህዳሴ ግድቡ መገንባትና አለመገንባት ላይ መጨቃጨቁ እንደማያዋጣ ተረድታ የመበጥበጥና የማደፍረስ ስልቷን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዙራለች፡፡ ዋና ግቧ ደግሞ ከህዳሴ የሚገኘውን ሀገራዊ ሀብት ኢትዮጵያ በአግባቡ እንዳትጠቀም ማድረግ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የባህር በር ለማግኘት በሚል ከሶማሌላንድ ጋር የተፈራረመችውን ስምምነት ተከትሎ በሞቃዲሾ ሶማሊያ እና በአዲስ አበባ መካከል ፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ውዝግብ ሲካሄድ መክረሙን ግብጽ እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ስትቋምጥለት የነበረውን የማደፍረስ ሥራዋን ለማከናወን ስትውተረተር ትታያለች። በቅድሚያ ግብጽ ከሶማሊያ ጋር ወታደራዊ ስምምነት አደረገች፤ ከዚያም የጦር መኮንኖችን እና ወታደራዊ አቅርቦቶችን የጫኑ ሁለት የግብጽ ወታደራዊ አውሮፕላኖች ሞቃዲሾ አስገባች፡፡

ኢትዮጵያ ይህ ጉዳይ አሳሳቢ ነው በማለት ስታመለክት፤ ግብጽ ጉዳዩ ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዳይሄድባት በማሰብ በሶማሊያ ውስጥ የየትኛውም ሀገር መንግሥት ወታደሮች አልገቡም፤ ‹‹ያያችሁበት ዓይን ግንባር ያድርገው›› በሚል ሁኔታ እንዲስተባበል አድርጋለች፡፡

የወታደሮቹን መግባት ያስተባበሉት ደግሞ የሶማሊያው ጠቅላይ ሚኒስትር ሐምዛ አብዲ ባሬ ማክሰኞ ጳጉሜን 5 ቀን 2016 ዓ.ም ሞቃዲሾ ውስጥ ባደረጉት ንግግር ነው፡፡ በንግግራቸው የትኛውም ሀገር ወደ ሶማሊያ ወታደሮቹን እንዳላስገባ ገልጸዋል። ሶማሊያ የውጭ ኃይሎችን ወደ ግዛቷ እንዲገቡ መፍቀዷ የአካባቢውን ሰላም እንደሚያናጋ በመግለጽ እርምጃውን ኢትዮጵያ በይፋ ተቃውማለች። ለሚመለከታቸውም አሳስባለች፡፡

የጦር መኮንኖችን እና ወታደራዊ አቅርቦቶችን የጫኑ ሁለት የግብጽ ወታደራዊ አውሮፕላኖች ሞቃዲሾ ማረፋቸው በስፋት ከተዘገበ በኋላ፤ ከኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከሶማሊያውን ጭምር ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ የሶማሊያ የተለያዩ ግዛቶች ባለሥልጣናት እና የፌዴራል መንግሥቱ ፓርላማ አባላትም መንግሥት የግብጽ ወታደሮች ወደ ሶማሊያ እንዲገቡ መፍቀዱን በይፋ ተቃውመዋል።

ለሶማሊያ መንግሥት መጠናከር እንዲሁም ለሶማሊያ ሕዝብ ሰላም መከበር ኢትዮጵያ የምትችለውን ያህል ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ እስከ ህይወት መስዋዕትነት የሚደርስ ዋጋ ከፍላለች፡፡ ከ15 ዓመታት በላይ ወታደሮቿን በሶማሊያ አሰማርታ የሀገሪቱን መንግሥት ስትደግፍ ቆይታለች። ሰላም ወዳዱና ቤተሰባዊ የሆነው የሶማሊያ ሕዝብ የተከፈለለትን መስዋዕትነት ባለመዘንጋት ለድርጊቱ ያሳየውን ተቃውሞ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ የሚያደንቁት ነው፡፡

ድሮም ቢሆን የሶማሊያ እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሰፊ በሆነ ድንበር ላይ ሲኖሩ የሚያመሳስላቸው ቋንቋ፣ ባህል እና ሃይማኖት ስላላቸው ተዋደውና ተቻችለው በሰላም የሚኖሩ ናቸው፡፡ ሊያለያዩዋቸው የሚሞክሩ አካላት ሲመጡ እንኳን በችግር ጊዜ ሲረዳዱ የሚስተዋሉ ናቸው፡፡ ቢሆንም በጥባጭ ካለ ጥሩ አይጠጣምና በሁሉም መስከ ጠንቀቅ ብሎ መጠበቁ ተገቢ ነው።

# ለብሔራዊ ጥቅም መከበር ያልሰራነውና መስራት ያለብን ምንድ ነው?

**ታምራት ተስፋዬ**

የአፍሪካ ቀንድ ጂኦፖለቲካ የየሀገሪቱ መሪዎችና ፖለቲካ በሞቀና በቀዘቀዘ ወቅት የተለያየ አሰላለፍ እየያዘ በተለያዩ ጊዜያት ከወቅቱ ጋር ይዘቱንና ቅርፁን ይቀያይራል፡፡ በየጊዜው ቀጠናውን እንቅልፍ ለመንሳት የሚደራጁና የሴራ አስፈፃሚነቱን ሚና የሚረከቡና እሳት ለኩሰው ቤንዚን የሚያርከፈክፉ ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ቀጠናው ላይ የሚንቀሳቀሱ የሽብር ቡድኖችም በትጥቅና በፋይናንስ የሚደግፋቸው አይቸገሩም፡፡

የአፍሪካ ቀንድ ከመልካምድራዊ፣ ጆኦ-ፖለቲካዊ፣ ስትራቴጂካዊ ፋይዳው አንፃር የሃያላን አገራት ጣልቃ ገብነት ጎልቶ ይታይበታል፡፡ ተገዳዳሪዎቹን አሜሪካና ቻይናን ጨምሮ በርካታ የሩቅና የቅርብ ተዋንያን የጦር ሠፈሮቻቸውን ያደራጁበትም ነው፡፡

የኢትዮጵያ ጂኦግራፊካል መገኛም በዚሁ የተጨነቀ ቀጠና መሃል Nucleus ውስጥ ነው፡፡ የዚህ የፖለቲካ ድባብና ሁኔታም አገሪቱም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ይነካካታል፡፡ ቀጠናው ላይ የተለኮሰ እሳት ኢትዮጵያንም ይጠብሳታል፡፡ ከጥንት እስከ ዘመናዊ የዲፕሎማሲ መስተጋብር የአገሪቱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማእከላዊ መሰረቶች ወይንም Determinant ዋነኛው ይህ ቀጠና ነው፡፡

ኢትዮጵያ በዚህ ውጥረት ለአፍታም በማይለየው ቀጠና ውስጥ ጥበብ በተሞላበት መልኩ ብሔራዊ ጥቅምን አስጠብቃ ዘመናትን አሳልፋለች፡፡ ይሁንና አገሪቱ ቀጠናው ላይ አቅም እንዳትፈጥር አለን የሚሉትን ሁሉ ለማዋጣት የሚሽቀዳደሙ አገራትም በቅርብም ሆነ በሩቅ በርካቶች ናቸው፡፡

አገሪቱ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታን ካስጀመረች ጊዜ አንስቶ ባለፉት ዓመታት ያሳለፈችባቸው አባጣና ጎርባጣ የበዛባቸው መንገዶችና በግልጽም ይሁን በስውር የሚስተዋሉ ሴራዎች የነገ ሃያልነትዋን በመረዳት አስቀድሞ ከማስቆም ጋር በእጅጉ የተሳሰሩ ናቸው፡፡

በተለይ ወደ ካይሮ ቤተመንግስት የሚገቡ ሰዎች ሁሉ የወንዙን ውሃ ባልተፈለገ መንገድ የፖለቲካ አጀንዳ በማድረግ፤ በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር ሊኖራቸው የሚችለውን ዘላቂ የጋራ ተጠቃሚነት ዕድል ትርጉም ወደሌለው የጠላትነት እና የግጭት መነሻ ለማድረግ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሲንቀሳቀሱ ታዝበናል፡፡

በተለይም የለውጡ መንግስት እጅግ ጥበብ በተሞላበት አካሄድ ሕዳሴ ግድብን ከምዝበራ እንዲሁም ግንባታውን ከሞተበት እንዲያንሰራራና ከሞት ተነስቶ የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ ማመንጨት እንዲሸጋገር ያተደረገበት ሂደት የካይሮውን መንግስት ከማስደንገጥ አልፎ ማመን ተቸግሮ እግሩ ወደ መራው እንዲሮጥ ሲያስገድደውም እየተመለከትን እንገኛለን፡፡

በቀጠናው በአህጉርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ተፅእኖ ፈጣሪ መሆን ከሁሉ ቀድሞ የሚያንጨረጭራቸው የፈርኦን ልጆች፣ ኢትዮጵያን የእድገት በሮች እግር በእግር እየተከተሉ መዝጋት የዘወትር መሻታቸው ስለመሆኑ ከቃላቸው በላይ ተግባራቸውም ምስክር ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ከሕዳሴ ግድብ ባሻገር የኢትዮጵያን የባሕር በር ፍላጎት ጥያቄ ተከትሎ ያስነሱት አቧራ በቂ ማስረጃ ሆኖ መቅረብ ይችላል፡፡

እንደሚታወቀው፣ኢትዮጵያ በሁሉም መስፈርት ትልቅ ሀገር ነች፡፡ የሚያሳዝነው ግን ከዓለም የባሕር በር/ወደብ ከሌላቸው ሀገሮች በሕዝብ ብዛት አንደኛ ነች፡፡ አገሪቱን ከቀይ ባሕርና ከወደብ ባለቤትነት ለመግፋት ከውስጥም ከውጭም የተሰራው ደባና ሴራ ሁሌም ቢሆን ትውልድን የሚያስቆጭ ነው፡፡

ወደብ ለአንድ ሀገር ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካው እድገት ወሳኝ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ባለከፍተኛ ኢኮኖሚ ባለቤት የሆኑ አገራት በሙሉ የወደብ ባለቤቶች ናቸው፡፡ ከድህነት አረንቋ ውስጥ ለመውጣት መተንፈሻን ማስፋት የግድ ነው፡፡

ኢትዮጵያን የባሕር በር ባለቤትነት መሆን ባለመቻሏ ኢኮኖሚው ክፉኛ ታፍኖ ቆይታል፡፡ ችግሩ አገሪቱ በየጊዜው ለወደብ ኪራይ ቢሊዮን ዶላሮችን እንድትከፍል ከማድረግ ባሻገር የምትፈልገውን ገቢና ወጪ ምርት አስተማማኝና ቀልጣፍ በሆነ መልኩ እንዳታስተላልፍ ማነቆ ሆኖባታል፡፡

ቀጠናው ላይ በዝሆኖች መካከል ግጭት ሲነሳም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያ እጅጉን ተጎጂ ናት፡፡ ይህ ደግሞ ባሕር በሩን ጥያቄ ከኢኮኖሚ ባሻገር ከሕልውና ከብሔራዊ ደህንነት ጋር በጥብቅ እንዲተሳሰር ያደርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ከሶማሊያ-ላንድ ጋር የተፈራረመችው የባሕር በር ስምምነትም ይህን እሳቤ መሰረት ያደረገ ነው።

**ከመሰል ቁልፍ ስራዎች ባሻገር የሕዝብ ግንኙነት ስራዎችን ያዝ ለቀቅ ሞቅ ደመቅ በሚል መልኩ ሳይሆን ወጥ በሆነና በተጠና መልኩ የኢትዮጵያን ሰላምና እድገት ፍላጎት እንዲሁም የአገርን ብሔራዊ ጥቅም ከቀጠናዊ እድገት ጋር ባቆራኘ መልኩ ዘወትር መከወንም የግድ ነው**

ኢትዮጵያ የባሕር በር የምታገኝበትን የመግባቢያ ሥምምነት የአገሪቱንን መጻኢ ዕድል የሚያሳምር ከመሆኑም በላይ ለዘመናት ወደብ አልባ ለሆነው ሕዝብ ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ የተገኘው የባሕር በር የኢትዮጵያን ስብራት የጠገነና የትውልድን የዘመን ቁጭት የመለሰ ነው፡፡ ለሀገራዊ ምጣኔ ሃብት ጡንቻ መፈርጠም እንዲሁም ለብሔራዊ ደህንነታ ዋስትን ያለው አስተዋጽኦ ነጋሪ የሚያሻው አይደለም፡፡

አንድ መታወቅ ያለበት ሀቅ ቢኖር ኢትዮጵያ የባህር በር ብታገኝ የሚጎዳው አካል የለም፡፡ የኢትዮጵያ ፍላጎትም በጋራ ማደግ፣ በጋራ መበልፀግ፣ በጋራ ደህንነትን ማስጠበቅ መሆኑን መረዳት የግድ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የአባይ ወንዝን በተለይም ግድቡም በሚመለከት የምታራምደው አቋም ከዚህ በተለየ መነፅር የሚታይ አይደለም፡፡

ይሁንና የመግባቢያ ስምምነቱን ተከትሎ የኢትዮጵያ እድገት የሚያርዳቸው አንዳንድ አገራት ከፍተኛ መደናገጥ ውስጥ የገቡ ሲሆን ‹‹እንዴት ተደርጎ›› በሚል አቧራ ለመስነሳት የቀደማቸው የለም፡፡ የመግባቢያ ስምምነት በአዲስ አበባ ሲፈረም ጨኸቷን የለቀቀችው ሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሐሰን ሼክ መሐመድም ኢትዮጵያ ላይ ተፅእኖ ለመፍጠር ከላይ እታች ሲሉ ከርመዋል፡፡

በሰኔ ወር ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አሕመድ (ዶ/ር) በፓርላማ ማብራሪያ ሲሰጡ የሶማሊያ መንግሥት አለመግባባቱን መፍታት ከፈለገ ከሞቃዲሾ ወደ አዲስ አበባ አንድ በረራ በማድረግ ብቻ በንግግር መፍታት እንደሚቻልና ከዚህ በተቃራኒ ከላይ እታች እያሉ የኢትዮጵያን ስም በማጥፋትም ሆነ የመንግሥት ላይ ጫና ለመፍጠር በመሞከር የሁለቱን አገሮች ችግር መፍታት እንደማይቻል አሳስበውም ነበር፡፡

ይሁንና አለመግባባቶችን በውይይት ከመፍታት ባለፈ የቬላ ሶማሊያ ሰዎች የዲፕሎማሲ ግንኙነትን እስከ ማቋረጥ የደረሰ እርምጃ መውሰዳቸውም ይታወሳል። አንዳንድ የሶማሊያ ከፍተኛ ባለሥልጣናት መደበኛም ሆነ ኢመደበኛ በሆኑ መንገዶች ኢትዮጵያን በተመለከተ የሚሰጧቸው መግለጫዎች መስረተ ቢስ ተራ ውንጀላዎች ከመሆን ባሻገር የሚያስተዛዝቡም ጭምር ሆነው አይተናቸዋል፡፡

ከሁሉ በላይ ግን በሰሶማሊያ የተሰማራው የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ኃይል አገሪቱን ለቆ እንዲወጣ ከመግፋት ባለፈ ጦሩ በግብፅ ሰላም አስከባሪ ኃይል እንዲተካ ለማድረግ መጠነ ሰፊ ቅስቀሳ ሲያደርጉ መመልከት እጅጉን አሳዛኝ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያውያን ለጎረቤት ሀገራት ችግር ቀድሞ መድረስ፤ የሌሎችን ችግር የራስ አድርጎ መመልከት በታሪካቸው ከሚታወቁበት አንዱ መገለጫቸው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ለሶማሊያ ሕዝብ ካለው ቅርበት /ወንድምነት/ የተነሳም ዓለም አቀፍ፤ አህጉራዊ እና አካባቢያዊ የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎችን ወስዶ ሕዝቡ ከጽንፈኛ እና ሽብርተኛ ቡድኖች የሚደርስበት ፈተና ለማቅለል፤ የተሻለ የሠላም አየር እንዲተነፍስ ለማስቻል ብዙ መስዋዕትነት የጠየቁ ወታደራዊ ተልዕኮዎችን ወስዶ በስኬት ተወጥቷል።

ሶማሊያ ሰላምና እንደ ሀገር መቆም የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ኃይል የከፈለው የሕይወት፣ የአካልና የንብረት መስዋዕትነት እጅጉን ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ እውነት ቆም ብለው ቢያስቡ የሶማሊያ መንግሥት አመራሮችም በቀላሉ ሊያስታውሱት የሚችሉት ነው፡፡ ይሁንና በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ማስታወስን የመረጡ አይመስልም፡፡

ኢትዮጵያ ይህንን ሁሉ ዓመት ውድ ልጆቻን ስትገብር የት እንደነበሩ የማይታወቁት ፈርኦኖችም ዛሬ ብቅ ብለው ‹‹ሞታችንን ከሶማሊያ ጋር ያድርገው›› እያሉን ነው፡፡ ከአራት አስርት ዓመታት በኋላም ሞቃዲሾ ተገኝተዋል፡፡

ምንም እንኳን ማንም አገር ከማንም ጋር ወዳጅነትም ሆነ ወታደራዊ ትብብር የማድረግ መብት ቢኖረውም፣ በተለይም ይህ አካሄድ በኢትዮጵያ ሠራዊት መስዋዕትነት እንደ አገር ለመቆም ስትውተረተር የኖረችውን ሶማሊያን የበለጠ አዘቅት ውስጥ የሚከት፣ በተለያዩ ግዛቶች እየተነሳ ያለውን ተቃውሞ በማጋጋል ከድኅረ ዚያድ ባሬ የባሰ ትርምስ የሚፈጥርና አልሸባብ ለተባለው አሸባሪ ኃይል አሳልፎ የሚሠጥ ነው፡፡

ይህ ቀድሞ የገባቸው ሶማሊያውያንም ለግብፅ ጓዳቸውን የከፈቱ የቪላ ሶማሊያ ሰዎችን በመቃወም ላይ ናቸው፡፡ አንዳንድ የሶማሊያ ግዛቶች ከወዲሁ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ መከላከያ ጋር መሆናቸውንና የግብፅ ጦር በግዛታቸው ድርሽ እንዳይል፣ የኢትዮጵያ ጦርም እንደማይወጣ እንቅጩን ለሞቃዲሾ ኤርፖርት መሪዎች በይፋ አሳውቀዋል፡፡ ይህን ተከትሎም የግብፅም ሆነ የሞቃዲሾ ሚሊሻ ቀጣይ ሕልውና ቅርቃር ውስጥ ገብቷል፡፡

ሶማሊያ መክተም ብቻውን ኢትዮጵያን አደጋ ላይ ለመጣል በቂ አለመሆኑ የገባት ካይሮ የተባበሩት መንግስታት (ተመድ) ደጃፍ መቆምም አላቋረጠችም። ለድርጅት የፀጥታው ምክር ቤትም በኢትዮጵያ ላይ ማንኛውንም ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ እንደምትችል የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጽፋለች፡፡

ይሁንና ምክር ቤት ካይሮ ‹‹ኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ላይ የምታደርገውን እንቅስቃሴ እንድታቆም ጫና አድርጉልኝ›› ስትል ያስገባችውን የክስ ደብዳቤ አልቀበልም በማለት አሳፍሯታል። ምክር ቤቱ የሕዳሴ ግድብን ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያ ሰላማዊ ድርድርን ለማድረግ ፍቃደኛ ሆና ሳለች፤ ውጥረትን መፍጠር እንደማያስፈልግና ጉዳዩ ደግሞ በአፍሪካ ሕብረት በኩል ለመፍትሔው የተሰራበት በመሆኑ እኛን አይመለከተንም በማለት እንደለመደችው ሕፍረቷን ተቀብላ እንድትመለስ አድርጓታል።

ኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማሳደር የካይሮ ወታደራዊ ስምምነትና ከበባ፣ ኢትዮጵያን ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የማቃቃር ሴራ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ሃሰተኛ ክሶች እንደ ትላንቱ ሁሉ ነገም ቀጣይ መሆናቸው የማይቀር ነው፡፡

ዋናው ቁም ነገር ግን እኛ ኢትዮጵያውያን ለአገራችን ብሔራዊ ጥቅም መከበር በአንድነት ለመቆም ምን ያህል ዝግጁ ነን፣ የአገራችን ፍላጎት በአንድነት መበልፀግ ስለመሆኑ በቅጡ ጉረቤቶቻችንም ሆነ ዓለም እንዲረዳው ምን ሰርተናል፣ ምንስ እየሰራን ነው? የሚለው ነው፡፡

አሁን ላይ ታሪካዊ ጠላቶቻችን እንቅልፍ እንደሌላቸው እያየን ነው፡፡ በአንደበታቸው ጭምር አገራችንን ለማተራመስ እንቅልፍ አጥተው እየተራወጡ መሆናቸውን እየነገሩንም ነው፡፡ ይህ በሆነበት እኛስ ምን እያደረግን ነው፡፡ ለብሔራዊ ጥቅም መከበር ያልሰራነውና መስራት ያለብን ምንድ ነው? ለሚለው ጥያቄ የምንሰጠው ምላሽም እጅጉን ወሳኝ ነው፡፡

ለባህራዊ ጥቅም መከበር ከሁሉ በላይ አንድነት ወሳኝ ነው፡፡ በአገር ጉዳይ ተቃራኒ አቋም መያዝ ለታሪካዊ ጠላት ያጋልጣል፡፡ ውስጣዊ ሰላሙን ያጣ አገር የውጭ ጥቃት መመከት አይቻለውም፡፡ አገርን ከሕልውና አደጋ መታደግ የሚቻለው ሕዝብና መንግሥት ሲናበቡ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ በሁሉም ጎራ ያሉ ኃይሎች ከእነሱ በላይ አገር እንዳለች ማወቅ አለባቸው፡፡ በውስጣዊ ጉዳዮች ስምምነቶች ባይኖሩም፣ በአገር ጉዳይ ግን አንድ መሆንና የውስጥ እንድነትን ማጠናከር ከሁሉም በላይ ለብሔራዊ ደኅንነትና ጥቅም በአንድነት መቆም የግድ ነው፡፡ በዚህ ወቅት የተለያዩ የዲፕሎማሲ አማራጮችን በመጠቀም የአገርን ጥቅም ለማስጠበቅ ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን፣ ውስጣዊ ሽኩቻን በመግታት አንድነትን ማጠናከር ለነገ የማይባል ጉዳይ መሆን አለበት፡፡

‹‹ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ›› እንደሚባለው፣ መንግስትም የአገራዊ አንድነት መደላድሉን በማመቻቸት፣ ጠላትን መግቢያና መውጫ ቀዳዳ ለማሳጣት በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ በየትኛውም ዘርፍ አገራቸውን ማገዝ ከሚችሉና የዳበረ ዕውቀትና ልምድ ካላቸው ዜጎች ጋር በቅርበት መስራትም ይኖርበታል፡፡

በረቀቀ ዲፕሎማሲና በበሰለ ፖለቲካ ጉዳዩን በአንክሮ እየቃኙ መራመድ በተለይ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራቶች ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊ ወዳጅነት ቀድሞ ከነበረው በተሻለ ለማጠናከር የሚያስችሉ ተግባራትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ከሶማሊያ ጋር የተፈጠሩ ችግሮችን በሰላማዊ የዲፕሎማሲ መንገድ መፍትሔ ለመስጠት የተጀመረውን ሥራ ዳር ማድረስም ተገቢ ነው፡፡

ሶማሊያ ሕዝብ ኢትዮጵያ ለሶማሊያ የክፉ ጊዜ ወዳጅ እንጂ ጠላት እንዳልሆነች የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎች መስራትና አሉታዊ ትርክቶችን የማስተካከል ስራ መስራትም ያስፈልጋል። ኢትዮጵያም ሆነች ሶማሊያ በአጠቃላይ የቀጣናው አገሮች ከመተባበር ውጪ መናቆር እንደማይበጃቸው አስረግጦ ማስገንዘብ ብሎም ድርድርና ንግግር መለመድ ያለበት የችግር መፍቻ ባህል እንዲሆን ማድረግም ይገባል፡፡

ከመሰል ቁልፍ ስራዎች ባሻገር የሕዝብ ግንኙነት ስራዎችን ያዝ ለቀቅ ሞቅ ደመቅ በሚል መልኩ ሳይሆን ወጥ በሆነና በተጠና መልኩ የኢትዮጵያን ሰላምና እድገት ፍላጎት እንዲሁም የአገርን ብሔራዊ ጥቅም ከቀጠናዊ እድገት ጋር ባቆራኘ መልኩ ዘወትር መከወንም የግድ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ብዙ ያልሰራነው አለና ትኩረት ሰጥተን ልንሰራበትም ይገባል፡፡ ሁሉም በየመስኩ በተለይ የኢትዮጵያ ፍላጎት በጋራ ማደግ፣ በጋራ መበልፀግ፣ በጋራ ደህንነትን ማስጠበቅ መሆኑን ደጋግሞ ማስገንዘብ ላይ የራሱን ጠጠር ሊወረውርም ይገባል፡፡


ሀገሪቷ በሕዝቦቿ ጥረትና ድጋፍ እየገነባች ያለችው የሕዳሴ ግድብ የሕልውናዋ መሰረትና የመሰረታዊ ፍላጎቷ ማሚያ በመሆኑ ግንባታን በፍጥነት ማጠናቀቅም የግድ ነው። ለዚህ ደግሞ መላው ኢትዮጵያዊ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁለንተናዊ ድጋፉን አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የዋግ ኽምራ- ከተረጂነት ወደ አምራችነት ጉዞ

**ማህሌት አብዱል**



የዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን የሚገኝና በተፈጥሮ ሃብቶቹም የሚታወቅ ነው፡፡ ብሔረሰብ አስተዳደሩ የተለያዩ ወረዳዎች ያሉት ሲሆን፣ 120 ሺ 638 ነጥብ 3 ሄክታር የሚታረስ መሬት አለው፡፡

ዞኑ ሰፊና ሁሉንም አይነት ሰብል ማምረት የሚያስችል ምቹ ስነ-ምሕዳር ያለው ቢሆንም፣ በተለያዩ ጊዜያት ባጋጠሙት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት ለድርቅ ሲጋለጥ ቆይቷል። በዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ማሕበረሰቡ በምግብ ራሱን ባለመቻሉ ለዓመታት በሴፊቲኔት እየተረዳ ለመኖር ተገዷል፡፡

በተለይም ለመሬት ሲባል በሚደረገው የደን ጭፍጨፋ የአካባቢው የተፈጥሮ ፀጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነ መጥቶ የሕዝቡን ችግር የከፋ እንዲሆን እንዳደረገው መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በፌደራልም ሆነ በክልል መንግስታት የተለያዩ የድጋፍ መርሃግብሮች ተነድፈው ማሕበረሰቡ ካለበት ችግር እንዲላቀቅ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ የብሔረሰብ አስተዳደሩም ቢሆን ካገጠሙትና እያጋጠሙት ካሉት ችግሮች ለመውጣትና ማሕበረሰቡን በተለይ በምግብ ዋስትና ራሱን እንዲችል ለማድረግ የተለያዩ የግብርና ልማት ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

የዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር የግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ አዲስ ወልዴ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ የብሔረሰብ አስተዳደሩ ዞኑን በመኸርና በመስኖ ማልማት የሚችልበት ሰፊ እድል አለው፡፡ በመኸር ከ120 ሺ 638 ሄክታር በላይ መሬት በማልማት 2 ነጥብ 3 ሚሊዮን ኩንታል ምርት የመሰብሰብ እንዲሁም በመስኖ ደግሞ 15 ሺ ሄክታር በላይ መሬት የማልማት አቅም አለው፡፡

ዞኑ በመሬትም፤ በምርትም ለክልሉ 2 ነጥብ 4 በመቶ ድርሻ አለው፤ ዋና ፀጋው ግን የእንስሳት ሃብቱ ነው፡፡ 821 ሺ 462 በግና ፍየል 383ሺ 359 የዳልጋ ከብት፣ የ7 ነጥብ 8 ሚሊዮን የንብ መንጋ መገኛ፣ በተከዜ ግድብ በዓመት ከዘጠኝ ሺ ቶን በላይ ዓሳ ማምረት የሚችል አቅምም አለው፡፡

እነዚህን ፀጋዎች በአግባቡ በማልማት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ አለመቻሉን ጠቅሰው፣ በዚህ የተነሳ አሁንም ዞኑ ከድህነት አዙሪት እንዲላቀቀቅ ማድረግ አለመቻሉን አመልክተዋል። የአካባቢውን የተፈጥሮ ፀጋ መሰረት ያደረገ፣ በብሄረሰብ አስተዳደሩ ችግር ስፋትና ጥልቀት ልክ ከችግር የሚያወጣ ስትራቴጂክ እቅድ በማዘጋጀት ለእቅዱ ተፈፃሚነት በየደረጃው ካለው አካል ጋር ልባዊ መግባባት ላይ በመድረስ የተለየ ስልት ቀይሶ መስራት የሚያሻው መሆኑን ያብራራሉ፡፡ በዚህ ረገድ በተለይም በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ አደጋ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ተቋቁሞ በምግብ ራስን ለመቻል ጥረት እየተደረገ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

ባለፉት ዓመታት በአካባቢው በተደጋጋሚ የተከሰተውን ድርቅ ከመከላከል ስራ ጎን ለጎን የአርሶ አደሩን የቴክኖሎጂና የግብዓት አቅም በማሳደግ ምርታማነት እንዲጎለብት አስተዳደሩ የበኩሉን ጥረት ማድረጉን ጠቅሰዋል፡፡ ለአብነትም በ2016/17 ምርት ዘመን 120 ሺ 638 ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዶ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ከዚህም ውስጥ እስካሁን 98 በመቶ የሚሆነው መሬት በዘር መሸፈኑን ይጠቁማሉ፡፡ በተመሳሳይ በምርት ዘመኑ በመስመር ለመዝራት ከታቀደው 3 ሺ 800 ሄክታር መሬት ውስጥ እስካሁን 97 በመቶውን ማሳካት መቻሉን ያስረዳሉ፡፡ ካለው የመስኖ አቅም 6 ሺ 39 ሄክታሩ እየለማ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም በብሔረሰብ አስተዳደሩ ዞን በተመረጡ ሶስት ሰብሎች 3 ሺ 551 ሄክታር በማልማት 86 ሺ 375 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ ‹‹እስካሁን በ93 ክላስተር በማደራጀት ከ3 ሺ 758 ሄክታር በላይ ማሳ በዘር መሸፈን ተችሏል›› ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በቡና እና በፍራፍሬ ልማት ደግሞ በምርት ዘመኑ 67 ሺ 600 ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ 85 ሺ 764 ችግኝ መዘጋጀት ተችሏል፤ ከዚህ ውስጥ ለተከላ የደረሱት 60 ሺ 614 ችግኞች ሲሆኑ፣ የእነዚህ ችግኞች ተከላም እስካሁን በ 104 ነጥብ 25 ሄክታር መሬት ላይ ተከላ ተካሂዷል፡፡

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ለብሄረሰብ አስተ ዳደሩ በክልል ግብርና ቢሮ ተገዝቶ መቅረብ ካለበት የአፈር ማዳበሪያ 69 ሺ119 ኩንታል ውስጥ 63ሺ168 ኩንታል ተገዝቶ ቀርቧል፡፡ ከዚህም ውስጥ 47ሺ 285 ኩንታል ወይም 75 በመቶ የሚሆነውን ለአርሶአደሩ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በዚህ ምርት ዘመን 9 ሺ 306 ኩንታል የተለያዩ የሰብል ዝርያዎችን የተመሰከረለት ዘር ለመጠቀም ታቅዶ እስካሁን ድረስ 9ሺ500 ኩንታል ጥቅም ላይ በመዋል ከእቅድ በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡ ይህም ሊሳካ የቻለው በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ትብብር ለአርሶ አደሩ እንዲሰራጭና ጥቅም ላይ እንዲውል በመደረጉ ነው፡፡

አስተዳደሩ ባለፉት አምስት ዓመታት ማሕበረሰቡ አሁን ካለበት ችግር እንዲወጣና ከተረጂነት እንዲላቀቅ ምርታማነትን በማሳደጉ ስራ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን መምሪያ ኃላፊው ይገልጻሉ፡፡ በተለይም በምግብ እህል ራሱን እንዲችል ለማድረግ እና ለዓመታት ስር ሰዶ የቆየውን የተረጂነት አስተሳሰብ ለመስበር ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ‹‹ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የብሔረሰብ አስተዳደሩ የአካባቢውን ምርታማነት በማሳደግ ከተረጂነት ለመላቀቅ ጥረት ማድረግ የጀመርነው፡፡ በወቅቱ ይህንን ከተረጂነት የመውጣት ዓላማ አንግበን ስራ ስንጀምር የለማው መሬት 764 ሄክታር ብቻ ነበር፤ አሁን ላይ ደግሞ 3 ሺ 758 ሄክታር ከፍ ማድረግ ችለናል›› ሲሉ ያመለክታሉ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የአርሶአደሩን የምርጥ ዘር አጠቃቀም ማሻሻል ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራቱን አቶ አዲስ ይናገራሉ፡፡ ‹‹በየዓመቱ እስከ ሶስት ሺ ኩንታል ነው ስንጠቀም የኖርነው፡፡ ባለፈው ዓመት ድርቅ የተከሰተበት አካባቢ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተለይ ዝቋላና አበርገሌ አካበቢዎች ዘር በማቅረብና ፕሮጀክቶችን በማስተባበር 9 ሺ 500 ኩንታል ምርጥ ዘር መጠቀም ችለናል›› በማለት ይጠቅሳሉ። ይህም የአርሶአደሩ የግብዓት አጠቃቀም እያደገ መምጣቱን እንደሚያመላክት ይገልፃሉ፡፡

‹‹ይሄ በቂ ነው ተብሎ ባይታሰብም፤ በሳይንሱ መሰረት ምርትና ምርታማነትን ከ50 በመቶ በላይ ለማሳደግ ምርጥ ዘር መጠቀም ያስፈልጋል›› ሲሉ ይጠቁማሉ፡፡ በተመሳሳይ የ2015/16 ዓ.ም 14 ሺ ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ጥቅም ላይ መዋሉን፤ ዘንድሮ ይህንን ቁጥር በሶስት እጥፍ በማሳደግ 47 ሺ ኩንታል ማዳበሪያ ጥቅም ላይ መዋሉን ነው ያስገነዘቡት፡፡

በሌላ በኩል አነስተኛና ኩታ ገጠም መሬት ያላቸውን አርሶአደሮችን በክላስተር በማደራጀት በጋራ ግብዓትና ምርጥ ዘር ተጠቅመው እንዲ ያመርቱ መደረጉንም አቶ አዲስ ጠቅሰዋል፡፡ ይህም የክላስተር ግብርና ልማት ስራ በአምስት ዋና ዋና ሰብሎች ላይ ያተኮረ መሆኑን፤ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ማሽላ፣ በቆሎ በደጋዎቹ አግሮ ኢኮሎጂ እንዲሁም በቆላዎቹ ደግሞ ማሽላን ጨምሮ እንቁ ዳጉሳና ማሾ የሚባሉ ሰብሎች እንዲመረቱ መደረጉን አቶ አዲስ ያብራራሉ፡፡

‹‹በዋናነት ግን አካበቢያችን ዝናብ አጠር እንደመሆኑ በአጭር ጊዜ የሚደርሱት እንቁ ዳጉሳና ማሾ ላይ ነው ትልቅ ትኩረት ሰጥተን እየሰራን ያለነው›› ይላሉ፡፡ እነዚህ ሰብሎች በተለይ የስርዓተ ምግብ ችግር ላለባቸው አካባቢዎች ጭምር አይነተኛ መፍትሔ ተደርገው እንደሚታሰቡ ያስረዳሉ፡፡ ‹‹እነዚህ አምስቱን ሰብሎች 3 ሺ በ551 ሄክታር ላይ ለማልማት ታቅዶ፣ እስከአሁን 3 ሺ 758 ሄክታር ማልማት ችለናል›› ሲሉ ይናገራሉ፡፡

እንደመምሪያ ኃላፊው ማብራሪያ፤ በዞኑ አትክልትና ፍራፍሬ ለማልማት ሰፊ አቅም ያለ እንደመሆኑ ይህንን አቅም በመጠቀም የምግብ ዋስትን ለማረጋገጥ እየተሰራ ላለው ሥራ አወንታዊ ሚና እንዲጫወት ለማድረግም ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ በ2016 ዓ.ም በክልል ደረጃ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት ከሌሎች አካባቢዎች አትክልቶች መምጣት ባለመቻሉ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ተፈጥሮ ነበር። ይህንን ችግር ለመፍታት አስተዳደሩ በአካባቢው ራሱን ችሎ እንዲያመርት በመደረጉ የሽንኩርትን ዋጋ ከ200 ብር ወደ 70 ማውረድ ተችሏል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ወደ መቀሌና ወደሌሎች አካበቢዎች ጭምር በመላክ አርሶአደሩ የገቢ አቅሙን እንዲያሳድግ ተደርጓል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎንም የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ስራ እየተሰራ መሆኑን አቶ አዲስ ይናገራሉ፡፡ ‹‹ሕዝቡን በማስተባበር በጦርነት ውስጥ የነበረውን ማሕበረሰብ ለ25 ቀናት በተከናወነ ተግባር ስነ-ልቦናውን በመቀየር ወደ ልማት እንዲገባ እየተደረገ ነው›› ይላሉ፡፡ ይህ ብቻ ግን በቂ አለመሆኑን፤ አሁንም በተለይ ከመሬት ወረራ ጋር ተያይዞ መሰረታዊ የሚባል የአመለካከት ችግር እንዳለ አመልክተዋል፡፡ በመሬት ወረራው የተነሳ የደን መመናመኑን በሚገባው ያህል መቀነስ አለመቻሉን ያስረዳሉ፡፡ ‹‹ይህም የመሬት ወረራ ተራራዎች እንዲራቆቱና የአፈር መሸርሸር እንዲመጣ አድርጓል›› በማለት ይጠቁማሉ፡፡

በሌላ በኩል በ2016/17 የምርት ዘመን ከስምንት ሺ ሄክታር በላይ በሚሆን መሬት ላይ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ጉዳት መድረሱን ጠቅሰው፤ በተለይ የክረምቱ ዝናብ ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዳህና እና ሰቆጣ ወረዳዎች ላይ ጉዳቱ የከፋ እንደነበር አመልክተዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም ተኪ ዘር እንኳን ለአርሶ አደሩ ማቅረብ ያለመቻሉን ያመለክታሉ። ‹‹በዋናነትም በዳህና ወረዳ ከፍተኛ ጉዳት በመድረሱ ከወረዳው ጋር በመጋገር አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በጀት በመመደብ ዘር እንዲገዙ በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ጥረት እያደረግን ነው›› ይላሉ። በዚህ ረገድም እንደዞንም ሆነ እንደ ክልል መሰል ችግር ሲደርስ ቶሎ ምላሽ የመስጠት ባህሉ ጉድለት እንደሚታይበት ተናግረው፣ ለዚህ ደግሞ የክልሉ የፀጥታ ችግር ዋነኛው ምክንያት እንደሆነ አንስተዋል፡፡

በመሆኑም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት፤ በተለይም አካባቢው አሁንም ቢሆን የምግብ ዋስትናን ያላረጋገጠ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ልዩ እቅድ ወጥቶና በጀት ተመድቦ የአርሶ አደሩን ዝቅተኛ ምርታማነት ሊያሻሽሉ የሚችሉ ሰፋፊ ፕሮጀክቶን በመንደፍ ድጋፍ ሊያደርጉ እንደሚገባ መምሪያ ኃላፊው ያስገነዝባሉ፡፡

‹‹በእርግጥ እንደመዋቅር እየተነጋገርን ነው፤ በክልል ደረጃ ቃል የተገቡልንና ተስፋ ሰጪ ነገሮች አሉ፡፡ ሆኖም እንደሃገርም ቢሆን ከድህነት ለመውጣትና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተለየ እቅድ ያስፈልጋል፤ ለዚህ ደግሞ ሁሉም ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል›› ሲሉ ጠቁመዋል፡፡ በተመሳሳይ የሰሜኑ ጦርነት በከፍተኛ ሁኔታ ያጠቃው እንደመሆኑ መልሶ እንዲያገግም ማድረጉ ላይም ሰፊ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

## አዳሪ ትምህርት ቤቶች-የዛሬ አበባዎች፤ የነገ ፍሬዎች ማዕከላት

ግርማ መንግሥቴ

ነገሩ «ሳይደግስ አይጣላም» ይመስላል። ባይሆን ኖሮ በአንዱ በኩል ሲያጋድል በአንደኛው ባልተቃናም ነበር።

የዚህ ጽሑፍ መነሻ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ስር የሚገኘው፣ መነሻ እድሜውን በ1923 ዓ.ም ያደረገው እቴጌ መነን የልጃገረዶች አዳሪ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ«እንኳን ደስ አላችሁ»ማስታወቂያ ሲሆን፤ እሱም የዘንድሮ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተፈታኞች ሙሉ ለሙሉ (100%) ማለፋቸውን አስመልክቶ «ተማሪዎች፣ የተማሪዎች ወላጆች፣ መምህራን እና የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች በሙሉ፤ እንኳን ደስ አላችሁ!!!» የሚል መልእክትና የተፈተኑና ያለፉ ተማሪዎችን በአግባቡ የተደራጀ ፎቶግራፍ በመያዝ ትምህርት ቤቱ በር-አጥር ላይ የተሰቀለው ነው።

እንደዚሁ ማስታወቂያ ከሆነ፣ መሀል ላይ ተቋርጦ የነበረው ይህ የልጃገረዶች ትምህርት ቤት በማሕበራዊ እና ተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፎች ተማሪዎችን የሚያበቃ ሲሆን፤ ከማሕበራዊ ዘርፍ ተማሪ ኮከብ አስቻለው ቢሆነኝ 554/600፤ እንዲሁም፣ ከተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ ሃሊማ ሲራጅ ተማም 518/600 በማምጣት ከየዘርፋቸው 1ኛ ወጥተዋል። እኛም ይህችን አጋጣሚ በመጠቀም በዝግጅት ክፍላችን ስም ሁለቱን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም «እንኳን ደስ አላችሁ!!!» ማለት እንወዳለን።

እንደ ምን ጊዜውም ሁሉ ዘንድሮም የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤት ይፋ ተደርጎ ነበር። ይፋ መደረጉን ተከትሎ ከአምናው «አስደንጋጭ» ውጤት ብዙም ከፍ ያላለ ውጤት የመገኘቱ ነገር ከሚመለከተው ትምህርት ሚኒስቴር ተሰማ። ውጤቱ አሳዘነም፣ አነጋገረም፣ አወያየም። ዝርዝሩን በተመለከተ ብዙ ስለተባለ ምንም ወዳልተነገረለት አዳሪ ትምህርት ቤት እንዝለቅ።

በርካቶች የመግቢያ ውጤት ባላገኙበት በዘንድሮው የ12ኛ ክፍል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ፈተና አዳሪ ትምህርት ተቋማት ግን «ሁሉም (100%) አልፈዋል» የሚለው ሰበር ዜናቸው ሆኖ ሰንብቷል። «ለምን?» በሌላ እትማችን የምንነጋገርበት ሆኖ ከውጤቶቻቸው ጋር የተያያዘውን ይዘታቸውን ብቻ እንመልከት።

### አስቀድመን የአዳሪ ትምህርት ቤቶችን ጥቂት መገለጫዎች እንመልከት::

ከሁሉም በላይ ከፍ ብሎ የሚሰማው የአዳሪ ትምህርት ተቋማት መገለጫ «ሕብረት» እና «እውቀት» ሳይነጣጠሉ አብረው የመሄዳቸውና በትምህርት ቤቶቹ በሕብረት መስራት፣ መረዳዳት፣ መተባበር መኖሩ፤ እንዲሁም፣ ጥልቅ እውቀት የሚገበይባቸው የመሆናቸው ጉዳይ ሲሆን፤ የተማሪዎች እንደ አንድ ቤተሰብ ሆኖ ለአንድ ዓላማ ሲባል የሚያከናውኗቸው ተግባራት መኖራቸው ነው።

ሌላው የአዳሪ ትምህርት ተቋማት መገለጫ የተጓዳኝ ትምህርት መኖር ሲሆን፤ በየዓመቱ፣ በዓመት ሁለት ጊዜ የጥያቄና መልስ ውድድሮች («በሁሉም» የሚለው አጠያያቂ ቢሆንም፤ በአዳሪ ትምህርት ተቋማት መካከል) ይደረጋል።

በከተማዋ የአዳሪ ትምህርት ቤቶች ሱፐርቫይዘር አቶ ይልማ ተሾመ እንደሚናገሩት ይህ የጥያቄና መልስ ውድድር በተማሪዎች መካከል ከፍተኛ የፉክክር መንፈስ ከመፍጠርም ባሻገር ተማሪዎች መምህራኖቻቸው በክፍል ውስጥ ያስተማሩትን ትምህርት ምን ይህል እንደተገነዘቡት ለማወቅ ከሚያግዙ የማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ ነው። የእነዚህና ሌሎች ቅንጅታዊ ተግባራት የዛሬ አበባዎችን ለነገ ፍሬነት ከማብቃት አንፃር እየተጫወቱ ያሉት ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

እነዚ ትምህርት ቤቶች ከአገራችንም ባለፈ ለሌላው ዓለም የሚተርፉ ተማሪዎችን (የነገ መሪዎችን) ማፍራት ከጀመሩ የሰነባበቱ ሲሆን፤ አንዱ ማሳያም በኤሮስፔስ ኢንጂነሪንግ ስማቸው ከሚጠራ የአሜሪካ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ቀዳሚ በሆነው፤ በአጠቃላይ በኢንጂነሪንግ ትምህርት ደግሞ አራተኛ ደረጃ ላይ በሚገኘው ጆርጂያ ቴክ ትምህርቱን በመከታተል ላይ ያለው መርሲሞይ መርጋ ነው።

“ቻይንኛም፣ አማርኛም የተማርኩት በአዳሪ ትምህርት ቤቱ ውስጥ ነው” ያለው መርሲሞይ ወደ አሜሪካ ለትምህርት ከማቅናቱ በፊት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን የተከታተለው በኦሮሚያ ልማት ማኅበርና አዳማ በሚገኘው ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት (በትምህርታቸው የላቁ ተማሪዎችን ከመላው ኦሮሚያ እየመለመለ በማስተማር በክልሉ ተጠቃሽ መሆን በቻለው) ነው። እድሉን አግኝቶ ወደ'ዚህ ተቋም ከመግባቱ በፊት ማጣሪያውን ማለፍ ነበረበት። በመሆኑም ወደ ተቋሙ ለመግባት ካመለከቱ (ከየአገራቱ) አቻዎቹ ጋር ተወዳድሮ ማለፍ ስለነበረበት ከ50,601 ተማሪዎች ጋር ለፈተና ተቀመጠ። አለፈ፤ ገባ። ትምህርትን በመከታተል ላይ ይገኛል።



የደሴ አዳሪ ትምህርት ቤት፣

«አንድን ትምህርት ቤት ጥሩ ትምህርት ቤት የሚያሰኘው ተማሪው ነው» የሚለውን የትምህርት ምሁራን አስተያየት በልባችን ይዘን ስንቀጥል፤ ሌላና የዚሁ ትምህርት ተቋም ፍሬ የሆነ ኮከብ የምናገኝ ሲሆን፣ እሱም ራጂ አሸናፊ ነው።

ስለ እሱ ለማወቅ ባደረግነው ፍተሻ ለማረጋገጥ እንደ ቻልነው፣ ራጂ አሸናፊ በ2014 ዓ.ም ከአዳማ ሳይንስ ኮሌጅ ሲመረቅ በፊዚክስ እና ሒሳብ የትምህርት መስኮች በአንድ ጊዜ ሁለት ዲግሪውን ማግኘት ብቻ ሳይሆን ስድሳ ትምህርቶችን «ኤ+» በማምጣት ነው ለማጠናቀቅ የቻለው። ራጂ የአሜሪካው አምአይቲ ዩኒቨርሲቲ በቀጥታ ሦስተኛ ዲግሪውን እንዲሰራ የሚያስችለውን ነጻ የትምህርት ዕድል ሰጥቶት በመከታተል ላይ ይገኛል። (ይህ ከፍተኛ ውጤት እያመጡ ወደ ሌሎች አገራት በመሄድ ከፍተኛ ትምህርትን የመከታተል ጉዳይ በሌሎችም የሚታይ ሲሆን፣ አንዱም በዚሁ ዓምድ ላይ መስክረንለት የነበረው፣ አዳሪ ትምህርት ቤት ያልሆነውና መሀል አራት ኪሎ የሚገኘው ኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ቀዳማዊ ምኒልክ ሼርድ ካምፓስ ነው።)

በባሕር ዳር ከተማ እንደ'ሚገኘው ስቴም ኢኖቬሽን ማዕከል፣ 100 ተማሪዎችን ብቻ ተቀብሎ የማስተማር አቅም ያለው፣ በስምንተኛ ክፍል ፈተና አማካኝ ውጤታቸው 85 እና ከዚያ በላይ የሆኑትን በመመዝገብ በሳይንስ ትምህርቶች፣ እንግሊዝኛ እና አማርኛን ጨምሮ ፈተና በመስጠት ያለፉትን የሚቀበለው የደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት፤ የወላይታው ሊቃ አዳሪ ትምህርት ቤት እና ሌሎች፤ እንዲሁም እንደ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ ትምህርት ቤት፤ የአዲስ አበባው ኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ቀዳማዊ ምኒልክ ሼርድ ካምፓስ ወዘተ ያስፈተኗቸውን ተማሪዎች በሙሉ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማብቃት የዛሬ አበባዎችን የነገ ፍሬዎች ለማድረግ በርትተው እየሰሩ ያሉ አዳሪ የትምህርት ተቋማት ናቸው።

በ2006 ዓ.ም የመጀመሪያዎቹን ተማሪዎች ተቀብሎ ማስተማር የጀመረው፤ በየዓመቱ 200 ተማሪዎችን የመቀበል አቅም ያለውና በ2014 ዓ.ም (የዘንድሮው መረጃ ስላልደረሰን ነው) የ12ተኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተናን በማስፈተን ተማሪዎቻቸውን ሙሉ በሙሉ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ካስገቡ ትምህርት ቤቶች መካከል አንዱ የሆነው የአዳማው ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት መርሲሞይ መርጋንና ሌሎችንም ለወግ እንዳበቃው ሁሉ ሌሎችም በዚሁ መንገድ እየተራመዱ ስለ መሆኑ ማሳያዎቹ ብዙ ናቸው።

ወላይታ ሊቃ ተማሪዎች በትምህርታቸው አቅም እያላቸው ነገር ግን በቤተሰቦቻቸው የኢኮኖሚ ሁኔታ የተነሳ ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘት ያልቻሉ ተማሪዎችን በወላይታ ልማት ማኅበር አማካኝነት ሙሉ ወጪያቸው ተሸፍኖ (በወጪ መጋራት የሚማሩ የተወሰኑ ተማሪዎችም አሉ) እንደሚማሩ፤ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ ማቱሳላ ቦና ከዓመት በፊት ከቢቢሲ ጋር ቆይታ ባደረጉበት ወቅት መናገራቸው የሚታወስ ሲሆን፤ ሌሎችም አወዳድሮ መቀበሉ እንዳለ ሆኖ፣ ይህንን የወላይታ ሊቃን አይነት ሰብአዊ ተግባር የአሰራራቸው አካል ቢያደርጉት ተቋሞቻቸውን ምሉእ ያደርግላቸዋል ብለን እናስባለን።

ከመላ አገሪቱ ከ50 በላይ ደረጃቸውን የጠበቁ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት እቅድ ይዞ እየሰራ መሆኑን ይፋ ያደረገው ትምህርት ሚኒስቴር በወቅቱ (2015 ዓ.ም) ይፋ ባደረገው መረጃ እንዳስታወቀው፣ ከአገር ውስጥ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆኑ፤ ከሚማሩት የሳይንስ እውቀት ባሻገር የማሕበረሰቡን ባሕል፣ እሴት እና ወግ ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ የሚያከብሩ እና የሚጠብቁ ዜጎችን ማፍራትን ዓላማ አድርገው የተቋቋሙና «ሥርቶ ማሳያ» የሆኑ አዳሪ ትምህርት ቤቶች ያስፈተኗቸውን ተማሪዎች በሙሉ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግባት የሚያስችላቸውን ውጤት አግኝተዋል።

ከባለፈው ዓመት መረጃ መረዳት እንደ ተቻለው፣ እነዚህ አዳሪ የትምህርት ተቋማት በየዓመቱ ተማሪዎቻቸው ከሚያስመዘግቡት የላቀ ውጤት በተጨማሪ አንድም ተማሪ በታሪክ ወድቆባቸው አያውቅም። ባለፈው ዓመት ከመገናኛ ብዙሀን ጋር ቆይታ አድርገው የነበሩት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ጥናት እና ምርምር ተቋም ዳይሬክተር የሆኑት በላይ ሐጎስ (ዶ/ር) ለሌሎች ተማሪዎች “ብቃት ምንድን ነው?” የሚለውን በማሳየት ረገድ ተምሳሌት የሚሆኑ ስለመሆናቸው መግለፃቸውም መነሻቸው ይሄው ስለ መሆኑ መጠራጠር አይቻልም። ተማሪዎቹ የተሰባሰቡት በፈተና ተለይተው በመሆኑ “አስተማሪ የማያውቀውን ጭምር አውቀው መገስገስ የሚችሉ መሆናቸውን መናገራቸውም እንደዛው።

አሁን ደግሞ «አሰራራቸው ምን ይመስላል?» የሚለውን እንመልከት።

የጋራ፣ አገራዊ የሆነ ደንብ፣ መመሪያና አሰራር ያላቸው የመሆኑ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ እያንዳንዳቸው ያጋራ የሆነውን የበለጠ የሚያዳብር የየራሳቸው አሰራር ሊኖራቸው የሚችል መሆኑ ተገማች ብቻ ሳይሆን ተጠባቂም ነው። እንደ ማሳያ ይሆነን ዘንድ አንዱን፣ የአዳማውን ብቻ ወስደን እንመልከት።

ተማሪዎች የሚኖሯቸውን ጥያቄዎች ያለምንም ችግር ማቅረብ የሚችሉበት የመማር-ማስተማር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን የሚያሳዩት ከተቋሙ የወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ መስከረም ወር ዓመቱ የትምህርት ካላንደር ሲጀመር የተማሪ ወላጆች እና ትምህርት ቤቱ ውል ይፈራረማሉ። ውሉም ተማሪው ውጤቱ ከቀነሰ እና በዓመቱ መጨረሻ አማካይ ውጤቱ ከ75 በታች ከሆነ የሚሰናበት መሆኑን የሚገልጽ ነው።

በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ውጤታቸው እንዳይቀንስ ተማሪዎቹን የሚያማክሩ መምህራኖች ተመድበው ለተማሪዎቻቸው እግር በእግር የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ። ይህ አይነቱ አሰራር አቻው በሆነው በወላይታ ሊቃ አዳሪ ትምህርት ቤትም በስራ ላይ እየዋለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ከመምህራን (በሙሉ ሁለተኛ ዲግሪ እንዲኖራቸው፤ በሁለተኛ ዲግሪያቸው 3.5 እና ከዚያ በላይ፤ በመጀመሪያ ዲግሪያቸው ደግሞ 3.00 ያስመዘገቡ እንዲሆኑ ይጠበቃል) ቅጥር ጀምሮ ጠንከር ያለ ሥርዓትን በሚከተሉት በእነዚህ አዳሪ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ መምህራን ተማሪዎቻቸው ለሚያነሷቸው፣ ለሚያቀርቡላቸው ማንኛውም አይነት ጥያቄዎች በማንኛውም ስፍራና ጊዜ መልስ ይሰጣሉ፤ ያስረዳሉ፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ያደርጋሉ። ወደ ደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ስናቀናም ተመሳሳይ አሰራር መኖሩን ነው የተገነዘብነው።

### ከቋንቋ አኳያ

የአዳማ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ተማሪዎቹ «ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍሎች የትምህርት ዕድል አግኝተው ሲሄዱ እንዳይቸገሩ» በማሰብ የተለያዩ የውጪ ቋንቋዎችን እንደሚማሩ ከቢቢሲ ጋር ቆይታ አድርገው የነበሩት (መርሲሞይ ከላይ “ቻይንኛም፣ አማርኛም የተማርኩት በአዳሪ ትምህርት ቤቱ ውስጥ ነው” ማለቱን ያስታውሷል) የተቋሙ ምክትል ኃላፊ፣ አቶ ደጀኔ የተናገሩ ሲሆን፤ «ከመማሪያ ቋንቋዎች ባሻገር አንድ ቋንቋ ጨምረው መማር ግዴታቸው ሲሆን፣ ከዚህ ውጪ ግን ያሉትን ቋንቋዎችን መርጠው ይማራሉ።» ሲሉም ነበር የተናገሩት።

“ሰባት ቋንቋዎችን የሚናገር ተማሪ አለን” ያሉት ኃላፊው በተቋማቸው ቻይንኛ፣ አረብኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዘኛ እና ኮርያኛ እንደሚሰጥም ነው የተናገሩት። ይህ፣ ከትምህርት ስርዓቱ፤ እንዲሁም፣ ከክፍለ ጊዜ ስርጭት ጋር ተጣጥሞ መሄድ ከቻለ፣ በእውነቱ የትምህርት ዓለም አቀፋዊነትን ከማሳየት አኳያ ተቋሙን ሊያስመሰግን የሚገባው ተግባር ነውና ሌሎችም - - - -

### የአዳሪ ትምህርት ቤቶች ሌላው መሰረታዊ ፋይዳ

ተማሪዎቹ ከሌሎች አጎራባች ትምህርት ቤቶች ካሉ ተማሪዎች ጋር ቢገናኙ፣ እነርሱ ለሌሎች የሚያካፍሉት እውቀት የመኖሩን ያህል የሚማሩት ነገር መኖሩ፤ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸው ተወዳድረው ወደ አዳሪው ትምህርት ቤት እንዲገቡላቸው በሚያደርጉት ፉክክር ውስጥ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ እንዲሰሩ እድል መስጠቱ፤ ለሌሎች ተቋማት አርአያ፣ ሞዴል በመሆን ልምድ የሚቀሰምባቸው ተቋማት መሆናቸው፤ ችግር ሆኖ ለቆየው የትምህርት ጥራት መምጣት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ መቻላቸው፤ ተማሪዎቹ ማሕበራዊነትን እንዲያጎለብቱ ማድረጋቸው ወዘተርፈ ሁሉ እነዚህን ተቋማት ልዩ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የነገ አገር መሪዎች መፍለቂያ ያደርጋቸዋልና ፋይዳቸው ከዚህ በመለስ ❖ ❖ ❖ የሚባል አይደለም እያልን፤ እስከ መጨረሻውም «ሙሉ ለሙሉ» (100%) የማሳለፉን ሙያ አጠናክረው እንዲቀጥሉበት፤ ሌሎችም አጥብቀው እንዲከተሏቸው፤ በየዓመቱ ከሚሰራጨው «አስደንጋጭ» የፈተና ውጤት ዜና ደመጣ እንዲገላግሉን አደራ እንላለን።

# «ኢትዮጵያ ትላንትም ዛሬም ስደተኞችን በአግባቡ የምታስተናግድ ሀገር ናት»

*-አቶ ብሩህተስፋ ሙሉጌታ*

**በስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር**

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

ስደት የሰው ልጆችን ለመከራ የሚዳርግ የኖረ ያለና ምን አልባትም የሚቀጥል ክስተት ነው። ሰዎችን በተለያዩ ምክንያቶች የትውልድ ቀዬያቸውን ጥለው በብዙ መከራና ስቃይ ውስጥ ርቀው እንዲሄዱ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች በርካቶች ናቸው። የሰላም እጦት፤ ስራ አጥነት፤ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ የፖለቲካ አለመረጋጋት ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል። ያም ሆነ ይህ በተለያዩ ምክንያቶች ሀገራቸውን ለቀው የወጡ ሰዎች መጠኑ ቢለያይም ለዘርፈ ብዙ አካላዊ፤ ስነ ልቦናዊና ሰብአዊ ጉዳት መዳረጋቸው አይቀሬ ነው። ለመከራ የሚዳርጓቸው አካላት ደግሞ በዋናነት ስደተኞችን በሕገ ወጥ መንገድ የሚያንቀሳቅሱ አካላት ቢሆኑም በየተጠለሉባቸው ሀገራት የሚገጥሟቸውም ችግሮች መኖራቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የስደተኞቹ እጣ ፈንታ የሚወሰነው በየደረሱበት ወይንም ጥገኝነት በጠየቁበት ሀገር ነባራዊ ሁኔታ ነው። የእነዚህ ሀገራት ያለበት የሰላም ሁኔታ፤ ስደተኞችን ተቀብሎ የሚያስተናግድበት ሕግና ትግበራ ነገሮችን በደግም ሆነ በክፉ የሚወስን ይሆናል። ለዚህም ነው አንዳንዶች ከሀገራቸው ብዙም ሳይርቁ በየጎረቤት ሀገራት የመከራ ጥግ የተባሉ ጥሩ ያልሆኑ ነገሮችን ለማስተናገድ ሲገደዱ የምናየው። ሌሎች ደግሞ ባሕር ተሻግረው ውቅያኖስ አቋርጠው የዓለም ዳርቻ የሚመስል ቦታ ደርሰው ስደት ከዘመድና ከወዳጅ ከመለየት ባለፈ እዚህ ግባ የሚባል ችግር ሳያደርስባቸው ይቀራል። ይልቁንም ያማረ የተሻለ ሕይወት መኖር ይጀምሩና በሀገራቸው ያሉ ወገኖቻቸውን ልብ ለስደት እስከ ማማለል ይደርሳሉ።

ኢትዮጵያ እንደሌላው ታሪኳ ሁሉ ስደተኞችን ተቀብሎ በማስተናገድ ረገድም ዓለም የመሰከረው የረዥም ዘመን ታሪክ ያላት ሀገር ናት። ስሟ የሚነሳው ደግሞ ከነገስታቷም ሆኑ ከሕህዝቦቿ ለእንግዶች በሚሰጡት ፍቅር ነው። ዛሬም ድረስ የኢትዮጵያ መንግስት የተለያያ ችግሮች ገጥመዋቸው ከጎረቤት ሀገራት የሚጎርፉትን ስደተኞች ስብእናቸውን ክብራቸውን ጠብቆ ለማስተናገድ በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል። የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግን ሀገሪቷ ስደተኞችን በመቀበል ብቻ ሳይሆን በመላክም ስሟ ሲነሳ ይስተዋላል። በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ መንገዶች ከሀገር ይወጣሉ።

የእነዚህም ኢትዮጵያውያን የመጨረሻ እድላቸው የሚወሰነው በየደረሰቡት ሀገር የእንግዳ ተቀባይነትና እነሱን የተመለከቱ ሕጎች ይሆናል። ባጭሩ ባሉበት ሀገር እንዲቆዩ አልያም ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ይደረጋል። በተመሳሳይ መንግስት በዚህ አይነት ከሀገራቸው የወጡ ኢትዮጵያውያንን ከስደት ተመላሾችንም ለማስተናገድ እየተሰራ መሆኑ ይታወቃል። እኛም ለዛሬው ዝግጅታችን በአሁኑ ወቅት በኢትይጵያ በዚህ ረገድ እየተከናወኑ ያሉ ስራዎችን አስመልክቶ በስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የጥበቃና ከስደት ተመላሾች ዘርፍ መሪ አቶ ብሩህ ተስፋ ሙሉጌታ ጋር የነበረንን ቆይታ እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል።



**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ስደተኞችን በማስተናገድ ረገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላት ተቀባይነት ምን ይመስላል ?**

**አቶ ብሩህ ተስፋ፡-** ስደኞችና ተመላሾች አገልግሎት በዋናነት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍና በአህጉር አቀፍ መድረክ የተቀበለቻቸውንና የፈረመቻቸውን ስምምነቶች መሰረት በማድረግ የሚሰራ ነው። ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ በሀገር ውስጥ የተዘጋጁ ሕጎች አሉ። እነዚህን መሰረት በማድረግ ነው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ስደተኞች ይስተናገዳሉ። እነዚህ ስደተኞች በሀገራቸው ጥበቃና ከለላ ሊደረግላቸው ያልቻሉና የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን ለማግኘት የጠየቁ ናቸው።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከለላና ጥበቃ እየተሰጣቸው ያሉት ስደተኞች ከሀያ ሰባት ሀገራት የመጡ ሲሆን ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ከጎረቤት ሀገራት የመጡት ናቸው። ስደተኝነት የሚሰጣቸው በአብዛኛው በተለያዩ ምክንያቶች ግጭቶችን ጨምሮ በሀገራቸው መንግስት ከለላ ማግኘት ላልቻሉ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያውያን የስደት ተመላሾችም የሚስተናገዱ ይሆናል። ኢትዮጵያዊ ከስደት ተመላሾች የሚባሉት በሌሎች ሀገራት በስደተኝነት ተመዝግበው ይኖሩ የነበሩ ናቸው። እነዚህን ስደተኞች በተመለከተ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የማድረግ በሀገር ውስጥ የሚኖራቸውን ቆይታና የማቋቋም ስራ ሁሉ የሚከናወነው በአገልግሎቱ በኩል ነው። አገልግሎቱ እነዚህን ስራዎች የሚያከናውነው ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ተቋማት ጋር በመቀናጀትም ነው።

**አዲስ ዘመን፤ ኢትዮጵያ ለስደተኞች የምትሰጠው ከለላና ጥበቃ ምን ይመስላል ?**

**አቶ ብሩህ ተስፋ፡-** ለስደተኞች ከለላና ጥበቃ ይሰጣል ሲባል በቀዳሚነት የሕግ ከለላን የአካል ጥበቃን ጨምሮ ለስደተኞች ተደራሽ ማድረግን ይመለከታል። ይህም የሚጀመረው ከምዝገባ ሲሆን ጥገኝነትም ሆነ ስደተኛ በሚለው የሚያገኙት መብት ተመሳሳይ ይሆናል። ከምዝገባው በኋላ በቀጥታ የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ የሚከናወን ይሆናል። ከዚህም ውስጥ የመጀመሪያው አገልግሎት መሰረታዊ ፍላጎት ማለትም የጤና፤ የትምህርት፤ ስራ የማግኘትን ማሟላት ነው።

ስደተኞች ጥበቃ የሚደርጋላችው በሶስት አይነት መንገድ ነው። አንደኛው በካምፕ ለብቻቸው አንድ ቦታ ሰፍረው እንዲቆዩ በማድረግ የመጠለያ፤ የንጽህና የምግብ አካላዊ ጥበቃ ይደረጋል። በቅርብ ርቅት ማሕበረሰብ የሚኖር ቢሆንም እነሱ የሚኖሩት ግን በተለየ ቦታ ብቻ ይሆናል። ይህም ማለት ስደተኞቹ በአንድ ግዜ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሆነው ወደሀገር ቤት ስለሚገቡ በተለየ ቦታ አስፈላጊው ሁሉ መሰረተ ልማት እንዲሟላ ተደርጎ የሚስተናገዱበት ነው። ከመጠለያ ባለፈ የራሳቸው የጤና፤ የትምህርት መሰረተ ልማቶች ይሟሉላቸዋል። ይህ የሚደረገው በድንበር አካባቢ ብዙ ግዜ በቂ መሰረተ ልማት ባለመኖሩና የስደተኞቹም ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ በሳይት ወይንም እንደገና ማስፈር የሚባለው ነው። እነዚህም በቀጥታ እንደመጡ የሚያርፉት ከማሕበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ በመሆናቸው የሚሰጣቸው አገልግሎት ከማሕበረሰቡ ጋር ተዳምሮ ይሆናል። የተሰጣቸውን መታወቂያና ሌሎች ዶክመንቶች መሰረት በማድረግ ጥበቃና ከለላን ጨምሮ ከማሕበረሰቡ ጋር በአንድ ላይ ይሆናል ማለት ነው። ለኑሮ የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶችንም በተመለከተ እንደ አዲስ መስራት ሳይሆን ያሉትን የማሳደግ ስራ ብቻ የሚከናወን ይሆናል። ለምሳሌ ስደተኞቹ የተቀላቀሉት ማሕብረሰብ ውስጥ ያለ አንድ ትምህርት ቤት ሶስት ሺ ተማሪዎችን የሚያስተናግድ ይሆናል። ተጨማሪ የትምህርት አገልግሎት የሚፈልጉ ሁለት ሺ ስደተኞች ቢጨመሩ እነሱን የሚችል ማስፋፊያ ይገነባል፤ ሌሎች የትምህርት ቁሳቁስና የሰው ኃይልም ይሟላል ማለት ነው።

ሶስተኛው የስደተኞች አጠባበቅ ደግሞ ከካምፕ ውጪ እንዲኖሩ የሚደረግ ሲሆን በከተሞች የሚተገበር ነው። በአዲስ አበባና ከዚህ ቀደምም በትግራይ መቀሌና ሽረ ላይ ይኖሩ እንደነበሩት ያሉትን የሚያካትት ይሆናል። እነዚህ ስደተኞች ራሳቸውን ማስተዳደር የሚችሉ መሆናቸውና ሌላ እነሱን ሊደግፍ የሚችል አካል ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሲኖር በጥገኝነት ለመኖር ጠይቀው እድሉ የሚሰጣቸው ናቸው። ነገር ግን እድሉ ራሳቸውን ማስተዳደር ስለቻሉ ወይንም የሚደግፋቸው አካል ስላለ ብቻ አይሰጣቸውም። የተለያዩ ተጨማሪ መስፈርቶች ያሉ ሲሆን የሚሰጠውም እድል ብዛት ውሱን ነው። ይህም ሆኖ የተለየ ከለላ ሊያስፈልጋቸው የሚሰጣቸው ሲሆን ሕክምና፤ የትምህርት እድል ዩኒቨርሲቲዎችን ጨምሮ ሊያገኙ የሚችሉበትም ሁኔታ አለ። በዚህ አይነት በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ብቻ የሚገኙት ስደተኞች ሰማኒያ አንድ ሺ ይደርሳሉ።

አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተም የመጠለያ፤ የምግብ፤ የውሃ የንጽህና መጠበቂያ፤ የጤና የትምህርት አገልግሎቶች ተደራሽ የሚደረጉት ከዓለም አቀፍ ድጋፍ አድራጊ ተቋማት ጋር በመሆንም ነው። ከትምህርት ጋር በተያያዘም በካምፕ ለሚኖሩ እስከ ሁለተኛ ደረጃ በዛው በካምፑ ውስጥ የሚሰጥ ሲሆን ከካምፕ ውጪ የሚኖሩት ደግሞ ከማሕበረሰቡ ጋር በአንድ ላይ ሁኔታዎች እየተመቻቹላቸው እድሉን የሚያገኙ ይሆናል። ሁለተኛ ደረጃና ከዛ በላይ ማለትም ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ከሆነ ግን ከኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ጋር ተወዳድረውና ተፈትነው ካለፉ እንደማንኛውም ዜጋ የሚስተናገዱ ይሆናል። በተመሳሳይ የጤና ጣቢያዎች በየካምፖቹ የሚዘጋጁ ሲሆን እነዚህ ተቀባይ ማሕበረሰቡንም የሚያስተናግዱ ይሆናል።

> **በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከለላና ጥበቃ እየተሰጣቸው ያሉት ስደተኞች ከሀያ ሰባት ሀገራት የመጡ ሲሆን ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ከጎረቤት ሀገራት የመጡት ናቸው**

**አዲስ ዘመን፤ ኢትዮጵያ ስደተኞችን የምታስተ ናግድበት መንገድ ከዓለም አቀፍ ሕጎች ጋር እንዴት ይታያል፡፡**

**አቶ ብሩህ ተስፋ፡-** በኢትዮጵያ ስደተኞች የሚስተናገዱት ጥሩ የሚባሉ የተዘጋጁ ሕግ መመሪያና ደንቦች አሉ። እነዚህ ሕግ መመሪያና ደንቦች ከዓለም አቀፍ ሕጎች ጋር የተናበቡና ዘመኑንም የሚዋጁ ናቸው። በዚህም መሰረት ኢትዮጵያ ለስደተኞች ከለላ ስትሰጥ የምታደርገው ምዝገባ በዓለም አቀፉ ደረጃ ለሚንቀሳቀሱት አካላት ተደራሽ ስለሚሆን ከለላውም ዓለም አቀፍ ይሆናል ማለት ነው። ኢትዮጵያ በተባበሩት

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# «ኢትዮጵያ ትላንትም ዛሬም...

ከገጽ 9 የዞረ

መንግስታት ድርጅት ስር ያለውን ቻርተር ሙሉ ለሙሉ ተቀብላ ፈርማለች። በመሆኑም አንድ ስደተኛ ኢትዮጵያ በሕጋዊ መንገድ ከተቀበለችው ግዜ ጀምሮ የተሰጠው ከለላና ጥበቃ ወደ ሌሎች ሀገራት ሲንቀሳቀስም እንደተጠበቀ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከስደተኞች ጋር በተያያዘ የሚካሄዱ መድረኮችን መሰረት አድርጎ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ የሚሰሩ ስራዎቸም ይኖራሉ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው ስደተኞችን የመቀበልና የማስተናገድ አካሄድ ከሌሎች ሀገራት አኳያ ሲታይ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል ?**

**አቶ ብሩህ ተስፋ፡-** ከሌሎች ሀገራት ጋር በማነጻጸር ኢትዮጵያ ስደተኞችን የምታስተናግድበት መንገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተቀመጡ መብቶች አኳያ ተቀራራቢ ነው ለማለት ይቻላል። ይህ የሚሆነው ደግሞ መጀመሪያ ስደተኞች በተጠለሉበት ሀገር በሚኖራቸው ቆይታ አካላዊ ስነ ልቦናዊና ሰብአዊ መብቶች መጠበቅ። ከዚህ ውስጥ ስነ ልቦናዊ ጥበቃዎችን በተመለከተ በአጋጣሚ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ስደተኞች አብዛኛዎቹ ቋንቋቸው በሀገር ውስጥም የሚነገር ነው። ይህም በማሕበረሰቡ ውስጥ የሚኖረውን ተመሳሳይና ተቀራራቢ ባሕልና ሀይማኖት ስለሚኖራቸው ግንኙነቱ የተስተካከለ እና ጠንካራ መስተጋብር ያለው ለማድረግ ትልቅ ፋይዳ አለው። በዚህ መስፈርት አሁን ያለውን ሁኔታ ስንመለከት በሀገር ውስጥ ካሉት ስደተኞች ትልቁን ቁጥር የሚይዙት ማለትም ሀምሳ በመቶ የሚደርሱት ስደተኞች ከደቡብ ሱዳን የተፈናቀሉ ናቸው። የደቡብ ሱዳን ስደተኞች ከጋምቤላ ጋር አኙዋክ እና ንዌር እንዲሁም ሙርሌ ጋር የሚመሳሰሉና አንድ አይነት ናቸው።

በሌሎቹም የሀገሪቱ ጠረፍ አካባቢዎች በሱማሌ ክልልና ሱማሊያ ሀገር በትግራይና በኤርትራ እንዲሁ ተመሳሳይ ነው። በመሆኑም አብዛኞቹ ስደተኞች በድንበር አካባቢ ከሀምሳ እስከ መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ለይ በጥሩ ሁኔታ ሲኖሩ ይታያል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንግዳ ተቀባይ መሆኑ ዓለም የመሰከረለት ሀቅ ነው። በሺዎች ዓመታት የሚቆጠረው የረዥም ዘመን ታሪኩም የሚያሳየው ይህንኑ ነው። በዚህም የተነሳ ዛሬም ድረስ ከየትም ሀገር መጥቶ ቢሆን ስደተኛ ሆኖ በየትኛውም የሀገሪቱ ክልል የሚንቀሳቀስ ሰው በማንነቱ የሚደርስበት ምንም አይነት መጥፎ ነገር ኖሮ አያውቅም። ለዚህም እንደ አንድ ጥሩ ማሳያ መጥቀስ የሚቻለው በኢትዮጵያ በስደት ወደ ሀገር ውስጥ በቅርብ ግዜ ከገቡትና እየገቡ ካሉት በተጨማሪ አርባ ዓመታት ድረስ የቆዩ እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በነጻነት የሚኖሩ ግለሰቦች ያሉ መሆናቸው አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- አገልግሎቱ ከስደት ተመላሾችን የሚያስተናግደው እንዴት ነው፡፡ ከስደት ተመላሾች የሚባሉት ኢትዮጵያውያንስ እነማን ናቸው፡፡**

**አቶ ብሩህ ተስፋ፡-** ከስደት ተመላሽ ተብለው የሚለዩት በሌሎች ሀገራት በስደተኝነት ተመዝግበው የነበሩና ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኙት ናቸው። እነዚህን ወደ ሀገር ቤት በመመለስም ሆነ ሀገር ውስጥ ከደረሱ በኋላ ሁኔታዎች ተመቻችተውላቸው የሚቆዩበትና በዘላቂነት መልሶ የማቋቋም ስራ የሚከናውንም ይሆናል። እነዚህ ስራዎች የሚከናወኑትም ከተለያዩ የባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ነው። በዚህ ሂደት የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ቀዳሚውን ድርሻ የሚይዝ ሲሆን ኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በየደረጃው የስደት ተመላሾቹ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን ቡድን አቋቁሞ የማረጋገጥ ስራ የሚያከናውኑ ይሆናል።

የስደት ተመላሾቹ በዚህ አካሄድ ኢትየጵያዊ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ሊሴ ፓሴ የይለፍ ፈቃድ ይሰጣቸዋል። ስደተኞቹ ወደ ሀገር ቤት ከገቡ በኋላ የመጀመሪያ ስራ የሚሆነው በግዜያዊነት የሚያርፉበት ቦታ ማመቻቸት ነው። ከዚህ በተጓዳኝ በግዜያዊነት በሚቆይበት ወቅት ኃይል ሰጪ ምግቦችን እንዲያገኙና የጤና አገልግሎትም እየተሰጣቸው ለአንድም ሆነ ለሁለት ወር ሁኔታዎች እንዲመቻቹላቸው የሚያደርግ ይሆናል።

ከዚህ በመቀጠልም ወደ ቀያቸው ተመልሰው በቋሚነት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ከሚያደርጉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባበር የሚሰሩ ስራዎች ይኖራሉ። ወደቀያቸው ከተመለሱ በኋላ ጥበቃና ከለላ ተደርጎላቸው እንዲቋቋሙ የሚሰሩ ስራዎች አሉ። ይህም የሚከናወነው በዋናነት በየአካባቢው ካሉ የስራና ክህሎት ቢሮዎች እና ከቴክኒክና ሞያ ተቋማት ጋር በመሆን ነው። በዚህም ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ የራሳቸውን ስራ እንዲሰሩ እንዲጀምሩ ሁኔታዎች የሚመቻቹላቸው ሲሆን በተጨማሪም በቆይታቸው ለእለት እለት እንቅስቃሴያቸው ቀጥተኛ ድጋፎችን በአይነትም ሆነ በገንዘብ እንዲያገኙ የሚደረግ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ያሉ ስተቶችን በተመለከተ በቂ መረጃ አይያዝም የሚል ሀሳብ ሲነሳ ይደመጣል፡፡ ይህንን እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ብሩህ ተስፋ፡-** መረጃ አያያዝን በተመለከተ ስራው የሚጀመረው የትኞቹም ስደተኞች ከየትም ሀገር ቢመጡ ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡበት ግዜ አንስቶ በሚደረግ ምዝገባ ይሆናል። ምዝገባው በተለያዩ ግዜያት እንደሁኔታው አራት ግዜ የሚከናወንም ይሆናል። የመጀመሪያው ምዝገባ እንደተከናወነ በኢትዮጵያ እንደ ስደተኛ መመዝገቡን የሚያረጋግጥለት ሰነድ ለስደተኛው ይሰጠዋል። እድሚያቸው ከአስራ አራት ዓመት በላይ ለሆኑትም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እስካሉ ድረስ ከላይ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች በሙሉ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው መታወቂያም ይሰጣቸዋል።

ምዝገባዎቹ ዳታዎችን ለማቀናጀት የሚጠቅሙ ሲሆን ይህንንም የሚሰጠውን አገልግሎት ፈጣንና ተደራሽ ለማድረግ ይረዳል። ከዚህ በተጨማሪ በእነዚህ ዳታዎች አማካኝነት ስደተኞቹ የልደት፤ የሞት፤ የጋብቻ፤ የፍቺና የመሳሰሉት የወሳኝ ኩነት ምዝገባዎች አገልግሎትም የሚያገኙ ይሆናል። ለተለያዩ ጉዳዮች ተፈልገው እነዚህ መረጃዎች ማረጋገጥ የሚፈልግ አካል ሲኖርም የማረጋገጥ ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል። እነዚህ አገልግሎቶች ተደራሽ የሚደረጉት ከኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎትና ስደኞችና ተመላሾች አገልግሎት በሕግ በተሰጡት ስልጣንና ኃላፊነቶች መሰረት ነው። መረጃዎቹም እንደየ ሁኔታው በየወቅቱ የሚታደሱ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ለስደተኞችና የስደት ተመላሾች የስራ እድል ከመፍጠር አኳያ ምን ምን ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡**

**አቶ ብሩህ ተስፋ፡-** ኢትዮጵያ የስደተኞችን ስራ የመስራት መብት በአዋጅ ያረጋገጠች ሀገር ናት። በዚህ ረገድ የሚፈጠሩ የስራ እድሎች በመሰረታዊነትን ስደተኞቹንም ተቀባዩንም ማሕበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ እንዲሆኑ ይጠበቃል። ይህ ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከተው የስራና ክህሎት ሚኒስትርን ሲሆን ከዚህ ጋር እና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር አገልግሎቱ የመግባቢያ ሰነዶችን ተፈራርሟል። ይህንን መሰረት በማድረግ የስራ ፈቃድ የሚሰጥ ይሆናል። በሀገሪቱ ያለው የስራ እድል በቂ ባለመሆኑና ዜጎችንም ሙሉ ለሙሉ ተደራሽ ማድረግ አለመቻሉ ይታወቃል። በመሆኑም የሚፈጠረው የስራ እድል ስደተኞችን መሰረት አድርጎ ነገር ግን ተቀባይ ማሕበረሰብንም ተጠቃሚ የሚያደርግ እንዲሆን ይጠበቃል። እንደ ሁኔታው ለተቀባዩ ማሕበረሰብ የሚሰጠው የስራ እድል ሀምሳ በመቶ አርባ ወይንም ሰላሳ በመቶ ሊሆን ይችላል። በዚህ አይነት የስራ እድል እንዲፈጠር ከዓለም አቀፍ አጋር ደርጅቶች ጋር በመሆን እየተሰራ ይገኛል።

ከስራ እድል ጋር ተያይዞ ሌላው ለስደተኞች የሚኖረው ተጠቃሚነት ራሳቸውን ችለው በተለያየ መንገድ ንግድን ጨምሮ በቅጥርም ሊሰሩ የሚችሉም ይኖራሉ። ነገር ግን ሁሉም ስደተኞች የእነዚህ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለመሆን በልዩ ሁኔታ የስራ እድሉን እንዲያገኙ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ራሳቸውን ችለው ለሚንቀሳቀሱ የንግድ ፈቃድ እንዲኖራቸው ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የሚሰሩ ስራዎችም አሉ። በአጠቃላይ ባለፈው ዓመት ብቻ ሰላሳ ሶስት ሺ የስራ እድል ተፈጥሯል። ይህ ሲሆንም ለተቀባይ ማሕበረሰቡ በሚሰባሰቡ እርዳታዎች የኢትዮጵያ መንግስት ከመቶ ሚሊየን ዶላር በላይ በቀጥተኛ ድጋፍ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ከዓለም ባንክ እንዲያገኝ ማድረግ ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- በሀገር ውስጥ በአንዳንድ አካባቢዎች የተፈጠሩ ግጭቶችን ተከትሎ ስደተኞች ለችግር እንዳይጋለጡ ምን ጥበቃ እየተደረገ ይገኛል፡፡ እስከ ቅርብ ግዜ በዚህ ረገድ በቂ ጥበቃና ከለላ እየተደረገ አይደለም በሚል ቅሬታ የሚያነሱ አሉ ለዚህ ጉዳይ ያለዎት ምለሽ ምንድን ነው?**

**አቶ ብሩህ ተስፋ፡-** በአንዳንድ አካባቢዎች እየተከሰቱ ያሉ ግጭቶች እንደ አካባቢው ማሕበረሰብ ሁሉ ስደተኞችንም መመልከቱ አይቀርም። ነገር ግን በተለይ ከአካላዊ ጥበቃ ከማድረግ አንጻር በካምፕ ከሆኑ በልዩ ሁኔታ ጥበቃና ከለላ የሚደረግላቸው ይሆናል። ከካምፕ ውጪ ከሆኑ ግን ጥበቃ የሚደረግላቸው ከማሕበረሰቡ ጋር ይሆናል። ይህም የሚደረገው በዋናነት በፌደራል ፖሊስ ሲሆን የክልል ጸጥታ አካላትም እንደየአስፈላጊነቱ የሚሳተፉበት አጋጣሚ ይኖራል።

በተጨማሪ በየአንዳንዱ ካምፕ ባሉ ብሎኮች ከራሳቸው ከስደተኞች የተውጣጡ ሰላም ለማስጠበቅ የሚንቀሳቀሱ የጸጥታ አደረጃጀቶችም ይኖራሉ። እነዚህም የውሎም ሆነ የአዳር ሁኔታዎችን በየእለቱ ለሚመለከተው አካል ተደራሽ የሚያደርጉ ይሆናል። ይህንን መሰረት በማድረግ መስተካከል ያለበትም ነገር ካለ ከአካባቢው አስተዳደሮች ጋር በመምከር በየወቅቱ ተገቢው ጥበቃና ከለላ የሚሰጥ ይሆናል። በቅርቡም በሱዳን የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ ከኢትዮጵያ ከለላ ለማግኘት የመጡ ለሱዳንና ጥቂት የሌሎች ሀገራት ዜጎች የኢትዮጵያ መንግስት በልዩ ሁኔታ የሰጠውና እየሰጠ ያለው ጥበቃ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው።

ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ለስደተኞች እየተደረጉ ያሉ ከለላንና ጥበቃዎችን በተመለከተ በአንዳንድ ሚድያዎች የሚነዙ ጉዳዮች እውነት አይደሉም። እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ስድተኞችን ዓላማ ያደረገ ጥቃት ተፈጽሞ አያውቅም። ከካምፕ ውጪ ሆነው በሚንቀሳቀሱበት ግዜ የሚፈጠር ነገር ቢኖር እንኳን ችግሩ ወይንም ጥቃቱ ስደተኞችን ብቻ የተመለከተ ሳይሆን ተቀባዩን ማሕበረሰብ የሚያካትት ይሆናል።

ይህም ሆኖ በአገልግሎቱ በኩል ስደተኞች ግጭቶችና አንዳንድ አስጊ ሁኔታዎች ሲኖሩ እንዳይንቀሳቀሱ ምክር ይሰጣል። በቅርብ ግዜያት በአንዳንድ ቦታዎች የነበሩ ግጭቶችን ተከትሎ ስደተኞችን ለመጠበቅ በተከናወኑ ስራዎች አስራ አንድ ፌዴራል ፖሊስ አባላት የሞቱ ሲሆን አስራ ሶስት ቆስለዋል። ከስደተኞች ወገን ግን አንድም ሰው ላይ ለጉዳት አልደረሰም ነበር።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ጥበቃና ከለላን በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች የስደተኞችን ብዛት የሚመለከቱም ናቸው። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ተቀብላ እያስተናገደቻቸው ያሉ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ቁጥሩ በየቀኑ የሚጨምር ቢሆንም እስካሁን ተመዝግበው ያሉት ከአንድ ሚሊየን አንድ መቶ ስልሳ ሺ በላይ ደርሰዋል። እነዚህን ሁሉ ስደተኞች በአግባቡ መያዝና ማስተናገድ የተቻለው በመንግስት በኩል ጠንካራ መዋቅርና የክትትል ስራዎች ማድረግ በመቻሉ ነው። በተጨማሪ እንደ ሴቶች ፤ ሕጻናት አካል ጉዳተኞችና ሌሎች ልዩ ጥበቃና ድጋፍ የሚደረግላቸው ስተደኞችም አሉ። ይህ የሚደረገውም በተለየ መንገድ ከሌላው በተለየ ለችግር ተጋላጭ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው። ለእነዚህ ስደተኞች ከልዩ ጥበቃና ከለላ ባለፈ የመሰረታዊ አገልግሎት ተደራሽ ሲደረግም ቅድሚያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም የምክርና የድጋፍ አገልግሎቶች እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ እንደትላንቱ ሁሉ ዛሬም ስደተኞችን በአግባቡ የምታስተናግድ ሀገር መሆኗ በግልጽ የሚታይ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- አመሰግናለሁ ፤**

**አቶ ብሩህ ተስፋ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

> **በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ተቀብላ እያስተናገደቻቸው ያሉ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ቁጥሩ በየቀኑ የሚጨምር ቢሆንም እስካሁን ተመዝግበው ያሉት ከአንድ ሚሊየን አንድ መቶ ስልሳ ሺ በላይ ደርሰዋል**

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ኢትዮጵያዊው የፋሽን ሳምንት

**ሰሚራ በርሀ**

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ እና በፋሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ ባሉ ተሳታፊዎች ዘንድ በጉጉት የሚጠበቁ የፋሽን ሳምንት ትርኢቶችና ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ፡፡ የኒውዮርክ ፋሽን ሳምንት፣ የበርሊን እንዲሁም ለንደን የፋሽን ሳምንቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚታወቁት የፋሽን መድረኮች ይጠቀሳሉ። በሀገራችንም ዲዛይነሮች የራሳቸውን ስራዎች ለማስተዋወቅ፣ የፋሽን ዲዛይን ማሰልጠኛ ተቋማትም ተማሪዎቻቸውን ሲያስመርቁ የፋሽን ዲዛይን ትርኢቶችን ሲያዘጋጁ ይስተዋላል፡፡

ማህሌት ተክለማርያም ትባላለች፡፡ ከሀገር ውጭ ለረጅም ጊዜ ቆይታለች፡፡ የሀብ ኦፍ አፍሪካ ፋሽን ሳምንት (HUB Of Africa Fashion week) መስራች እና አዘጋጅ ናት፡፡ እሷ እንዳለችው፤ የፋሽን ሳምንቱ የተመሰረተው ከ15 ዓመት በፊት እ.አ.አ በ2010 ነው፤ የተመሰረተበት ዓላማም ለፋሽን ዲዛይነሮች መድረክ መስጠት እና ኢንዱስትሪውን ማሳደግ እና ይበልጥ ማስተዋወቅ ነው፡፡

የፋሽን ሳምንቱን ለመጀመር ስታስብ ከሀሳቧ ተጋሪ ኬንያዊት ጋር መምከሯን ማህሌት ጠቅሳ፣ ሀሳቡም በሌላው ዓለም የሚታወቁት የፋሽን ሳምንት ትርኢቶች ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ አፍሪካ ውስጥ እንዲካሄዱ መፈለግ እንደነበር ታስታውሳለች፡፡

የመጀመሪያው የሀብ ኦፍ አፍሪካ ፋሽን ሳምንት 12 ዲዛይነሮችን ማሳተፉን ትገልጻለች፡፡ እነዚህም ስድስት ከኢትዮጵያ ሌሎች ስድስቱ ደግሞ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የተወጣጡ እንደነበሩም አስታውሳለች፡፡

ለፋሽን ሳምንቱ ‹‹ሀብ ኦፍ አፍሪካ›› የሚል ስያሜ የተሰጠውም የአፍሪካ መዲና የሚል ስያሜ ባላት አዲስ አበባ አህጉረ አፍሪካን በሚመለከቱ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውይይቶች የሚደረጉና ውሳኔዎች የሚተላለፉ በመሆናቸው ነው ብላለች፡፡



**ማህሌት ተክለማርያም፣**

አብዛኛውን ጊዜዋን በኒውዮርክ እና ቨርጂኒያ ያሳለፈችው ማህሌት፣ በማርኬቲንግ እና ቢዝነስ ላይ ትምህርት መከታተሏንም ገልጻለች፡፡ ‹‹ስንጀምረው የነበረው ዝግጅት ለሁለትና ሶስት ቀና የሚካሄድ ነበር፤ ከዚያም እያደገ ሄደ፡፡ አሁን የፋሽን ትምህርት ቤቶችም ስለበዙ ያለው እንቅስቃሴ በፊት ከነበረው አድጓል ማለት እችላለሁ፡፡›› በማለት ትገልጻለች፡፡

‹‹የፋሽን ኢንዱስትሪው በአፍሪካም ጭምር አድጓል›› የምትለው ማህሌት፣ በናይጄሪያ የሚዘጋጀውን ሌጎስ ፋሽን ሳምንትን፣ የደቡብ አፍሪካው ፋሽን ትርኢትን /ከ20 ዓመት በላይ ያስቆጠረ / እና በሴኔጋል የሚካሄደው ዳካር ፋሽን ሳምንትን ለእዚህ እንደ አብነት ይጠቀሳሉ። ‹‹እኛ በይበልጥ ዘርፉ ላይ ለተሰማሩ ዲዛይነሮች እድል መፍጠር ላይ እንሰራለን›› ብላለች፡፡

የፋሽን ኢንዱስትሪ ከፍተኛ አቅም እና ፈጠራ የሚገኙበት መሆኑን ጠቅሳ፣ ‹‹ አቅም እና ችሎታ እያላቸው ገበያው ላይ መቆየት ባለመቻላቸው ከገበያው የሚወጡ እንዳሉም ጠቅሳ፣ ስለዚህ በመንግስት ደረጃም ድጋፍ ሊደረግ እንደሚገባም አስገንዝባለች። ይህንን ዘርፍ ለመደገፍ የተቋቋመ የፋሽን ዲዛይን ማህበር ከባሕልና ቱሪዝም እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር እየሰራ እንደሚገኝም ገልፃለች።

በሀብ ኦፍ አፍሪካ የፋሽን ሳምንት ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የሚመጡ ዲዛይነሮች ተሳታፊ ይሆናሉ። ‹‹ያለፈው ሀብ ኦፍ አፍሪካ ላይ ከ25 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊ ዲዛይነሮች እና ከናይጄሪያ፣ ጋናም እንዲሁም ሌሎች ዲዛይነሮች ይሳተፋሉ›› ብላለች፡፡

እሷ እንዳለችው፤ የፋሽን ሳምንቱ ቀደም ሲል በጥቅምት ወር ይካሄድ ነበር፣ የብዙ ዲያስፖራዎች እንቅስቃሴ በጥር ወር መሆኑ ታይቶ ዝግጅቱ የሚካሄድበት ወቅት ወደ ጥር ወር ተዛውሯል። በፋሽን ሳምንቱ ላለፉት 15 ዓመታትም ወደ 200 የሚጠጉ ዲዛይነሮች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ‹‹ ፋሽን ኤግዚቢሽን ብለን ጀማሪ ዲዛይነሮችን እናሳትፋለን፤ ኢንዱስትሪው ላይ የቆዩ ዲዛነሮች ደግሞ በፋሽን ትርኢቱ ላይ ይሳተፋሉ›› ብላለች፡፡

ሀብ ኦፍ አፍሪካ ፋሽን ሳምንት በውስን ሙያዎች የተገደበ እንዳልሆነም ጠቅሳ፣ የጸጉር ሙያ ባለሙያዎች፣ የሜካፕ አርቲስቶች፣ የፋሽን ዲዛይነሮችና የፋሽን ፎቶግራፍ ባለሙያዎች የሚሳተፉበት መሆኑን አመልክታለች፡፡

በመድረኩ ስራቸውን ለሚያቀርቡ ፋሽን ዲዛነሮች በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት ምዝገባ መጀመሩንም ጠቁማለች፡፡ ሀብ ኦፍ አፍሪካ የራሱ የቦርድ አባሎች አሉት፤ እነሱም ዲዛይነሮች የሰሯቸውን ስራዎች በመመዝገቢያ ቅጹ ላይ በፎቶ አድርገው ይልኩልናል፤ በአካል ማየት የምንፈልገው ስራ ከሆነ ደግሞ እንዲያመጡልን አድርገን እንገመግማለን፤ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የምንጋብዝ ከሆነ ደግሞ ከገጾቻቸው ላይ ስራቸውን ለማየት እንሞክራለን ፡፡ ›› ብላለች፡፡

ስለፋሽን ሳምንቱ እንዳብራራችውም፤ በአሁኑ ወቅት በዚህ ዘርፍ የሚሳተፉ ዲዛነሮችም ሆኑ ሞዴሎች በርከት እያሉ መጥተዋል፤ እንደ አንድ መድረክ ለዲዛይነሮች ራሳቸውን ማስተዋወቂያ መንገድ ነው፤ በቦታው ለሚገኙ ታዳሚዎች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ መገናኛ ብዙሀኖች ፋሽን ላይ ብቻ ተመርኩዘው የሚሰሩ መጽሄቶች ላይ የሚዲያ ሽፋኖችን ስለሚያገኙ የመታየት እድል አላቸው፡፡ በተጨማሪም በፋሽን ሳምንቱ ደግሞ በቀጥታ ከደንበኞች ጋር ስራቸውን ከወደዱ ሰዎች ጋር እንዲገናኙ እናደርጋለን ብላለች፡፡

በፋሽን ሳምንቱ ላይ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ተጋባዥ እንግዶች ጋር በመሆን ውይይቶች ይደረጋሉ፤ ይህም ለዲዛነሮች ተጨማሪ ግብዓት ይሆናል፤ በስራቸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ነው ፡፡

የዘንድሮውን የሀብ ኦፍ አፍሪካ ፋሽን ሳምንትን ለማዘጋጀት ዲዛይነሮችን በመቀበል ላይ መሆኗን ጠቅሳ፣ የወደፊት እቅዱ ከዚህ የበለጠ እንደሚሆን ገልጻለች፡፡ ‹‹ የፋሽን ሳምንት ብሎ ማዘጋጀት የራሱ የሆነ ውጣ ውረድ አለው፤ አቅምና ዝግጅትን ይጠይቃል፡፡ እኔም ከዚህ በላይ አቅም ያለው እንዲሆን አፈልጋለሁ›› ብላለች፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ትኩረት ለሙያ ትምህርቶች

**ዋሰልኝ አየለ**

የመስከረም ወር የትምህርት መጀመሪያ ወር ነውና ትምህርታዊ አጀንዳዎች ይበዛሉ፡፡ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የተለመደው የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ እንዲሁም የቅድመ ምረቃ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ብቻ አይደለም አጀንዳ የሆነው፡፡ የድህረ ምረቃ ትምህርትም የመስከረም ወር አጀንዳ መሆን ጀምሯል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው የትምህርት መመሪያ መሰረት የድህረ ምረቃ ትምህርት በብሔራዊ ፈተና መልክ መሰጠት መጀመሩ ነው። ከዚህ በፊት ዩኒቨርሲቲዎች በራሳቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየፈተኑ ያስተምሩ የነበረበት አሰራር ቀርቶ ከባለፈው ዓመት ጀምሮ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ሆኗል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሰሞኑን የዚህን ፈተና የጊዜ ሰሌዳ የያዘ ሰነድ ሲያሰራጭ ተመልክተናል፡፡ በአጠቃላይ መስከረም ወር የትምህርት አጀንዳ ነው።

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አንድ ልብ ያልተባለ ነገር አለ፡፡ ይሄውም የሙያ ትምህርት ነው፡፡ የሙያ ስል የተለመዱትን የሕክምና፣ የምሕንድስና.... አይነት ትልቅ ትኩረት የተሰጣቸውን ማለቴ አይደለም። የእጅ ሙያ ትምህርት የሆኑት ናቸው ትኩረት ያልተሰጣቸው፡፡ በተለምዶ ቴክኒክና ሙያ እየተባሉ የሚጠሩት ማለት ነው፡፡ ቴክኒክና ሙያ ውስጥ አሉ የሚባሉት ራሱ አገር በቀል የሆኑ የእጅ ሙያ ትምህርቶች ትኩረት የተሰጡበት አይመስልም። ምክንያቱም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ የሸክላ ሥራ፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ ሥራ፣ የባሕላዊ መሳሪያዎች አሰራር የመሳሰሉት ሲወራባቸው አይሰማም፡፡

የአንዲት አገር የሥልጣኔ እና የዕድገት መገለጫ ኢንዱስትሪ ሆኗል፡፡ የትልልቅ ኢንዱስትሪዎች መነሻ ደግሞ የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡ የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ደግሞ እነዚህ አገር በቀል የሆኑ የማሕበረሰቡ የእጅ ሥራዎች ናቸው፡፡ እነዚህ አገር በቀል የጥበብ ሥራዎች በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ደረጃ ትኩረት ቢሰጣቸው ወደ ዘመናዊነት ያድጋሉ። ፈጠራ ፈጠራን እየወለደ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ይሆናሉ።

ሰዎች ለሥራ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ሲሄዱ፤ ከሄዱበት አካባቢ ያለ ባሕላዊ የመገልገያ ዕቃ ይገዛሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከዘመናዊ የፋብሪካ ዕቃዎች በተሻለ የሚወደዱ እና የሚፈለጉ ባሕላዊ ዕቃዎች አሉ። እነዚህ ዕቃዎች የተሰሩት ከዋናው ጥሬ ዕቃ በባሕላዊ መንገድ ነው፡፡ እነዚያን ዕቃዎች የሰሩ ሰዎች ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ አይደሉም። በልማዳዊ መንገድ ነው የሰሩት፡፡ የሰሩት ሰዎችም እንደ ባለሙያ ሳይሆን የሚታዩት እንደ ኋላቀር ነው፡፡ ከእነዚያ ባለሙያዎች ይልቅ ለአገር ምንም ጠብ ያላደረገ ዲግሪ የደራረበ ሰው ይከበራል፡፡

እውነታው ግን በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ‹‹የተማረ›› ከሚባለው ዜጋ ይልቅ ዘመናዊ ትምህርት ያልተማረው ለኢንዱስትሪ ግብዓቶች ይቀርባል። ለምሳሌ፤ የግብርና መገልገያ ዕቃዎች አሁንም በባሕላዊ መንገድ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ የተማረ የሚባለው ግን ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎችን መገጣጠም አልቻለም። እነዚያው ጥቂቶችም ቢሆን ከውጭ የሚመጡ ናቸው፤ ለዚያውም በብዛት የሉም፡፡

ለመስክ ሥራ በምንሄድባቸው የገጠር አካባቢዎች ብዙ የዕደ ጥበብ ሥራዎች ይገኛሉ። የተማረ የሚባለው የሕብረተሰብ ክፍል እነዚህን ዕቃዎች ይገዛል፤ እሱ ግን የመገልገያ ዕቃዎችን በዘመናዊ መንገድ ማምረት የሚያስችል ክሕሎት የለውም፡፡ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ ብቻ ሳይሆን የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ሁሉ ከውጭ የሚመጡ ናቸው፡፡ መዘመን እና መሰልጠን የተባለው እነዚህን የፈረንጅ ምርቶች መግዛት ነው። በአንፃሩ በአገር በቀል ጥበብ የተሰሩት ዕቃዎች የኋላቀርነት መገለጫ ተደርገው ይታያሉ፡፡

እርግጥ ነው አንዳንድ ባሕላዊ ዕቃዎች በጥንካሬም ሆነ በአገልግሎት ፍጥነት ከፈረንጅ ምርቶች ያነሱ ናቸው፡፡ ዳሩ ግን በሥርዓተ ትምህርታችን ውስጥ ተካተው ትኩረት ቢሰጣቸው የመዘመን ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ የእጅ ሙያ ትኩረት ቢሰጠው በራሱ እየዳበረ ይሄድ ነበር፡፡ ባሕላዊ ዕቃዎችን የሚሰሩት ሰዎች ራሱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻሉት ይሄዳሉ፡፡ ስለዚህ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና ትኩረት የሚሰጠው ቢሆን ይዳብር ነበር ማለት ነው፡፡

ቀደም ሲል በነበሩት ጊዜያት ‹‹የእጅ ሥራ›› የሚባል የትምህርት አይነት ነበር፡፡ ቢሆንም ግን በቂ ትኩረት የተሰጠው አልነበረም፤ የንድፈ ሀሳብ ትምህርት የለውም፡፡ ተማሪዎች የሚችሉትን የእጅ ሥራ ይዘው እንዲመጡ ይደረጋል፡፡ አንዳንዱ የግብርና መሳሪያዎችን ይሰራል፣ አንዳንዱ የጦር መሳሪያ ይሰራል፣ አንዳንዱ የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ይሰራል፡፡ የመጨረሻ ግቡ ግን የቁጥር ነጥብ ለማግኘት ብቻ ነው፡፡ ተማሪው በዚያ ሙያ የመቀጠል ፍላጎት የለውም፤ ምክንያቱም ያ ሙያ እንደ ትልቅ ሙያ የሚቆጠር አልነበረም፡፡ ይህ ችግር እነሆ አሁን ድረስ ስለዘለቀ አሁንም የእጅ ሙያ በትምህርት ውስጥ ትኩረት ሲሰጠው አይታይም፡፡

ከሦስት ዓመት በፊት ይመስለኛል የኦሮሚያ ክልል መንግሥት በቡራዩ አካባቢ የእጅ ሙያ ትምህርት ቤት አስገንብቶ ሲያስመርቅ አጀንዳ ሆኖ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ በወቅቱ ብዙ ሰዎች አድንቀዋል፡፡ ምክንያቱም የዘመናዊ ኢንዱስትሪ መነሻው የአካባቢ የእጅ ሙያዎችን ማዳበር ነው፡፡ ይህ የኦሮሚያ ክልል ጅማሮ ግን በአገር አቀፍ ደረጃ አጀንዳ ሲሆን አላየንም።

አሁንም ትምህርት ሲባል ያው የተለመደው የአውሮፓ ሳይንቲስቶችን ስም እና ንድፈ ሀሳብ መሸምደድ ነው ትኩረት የሚሰጠው። ጎበዝ ተማሪ የሚባለውም ያንን ሸምድዶ ከፍተኛ ቁጥር ሲያስመዘግብ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ከሚታዩ የጎበዝ ልጆች የፈጠራ ሥራዎች በስተቀር ተግባር ተኮር ውጤት አልታየም፡፡

ይባስ ብሎ እንዲያውም የእጅ ሙያ ያላቸው ልጆች እንደ ሰነፍ የሚታዩበት አጋጣሚም አለ፡፡ የተለመደው ጎበዝ ተማሪ ማለት ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ፣ ባዮሎጂ፣ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ.... ሸምድዶ ከፍተኛ ቁጥር የሚያመጣ ነው፡፡ የፊዚክስ ውጤት የሆነውን አንድ ቀላል ማሽን ከመሥራት ይልቅ የፊዚክስ ንድፈ ሀሳብ ሸምድዶ ከፍተኛ ቁጥር ማምጣት የተሻለ ጎበዝ ተማሪ ያሰኛል፡፡ ከዚህ ልማድ መላቀቅ አለብን፡፡

ይህ ይሆን ዘንድ ለእጅ ሙያ ጥበቦች ትኩረት መሰጠት አለበት፡፡ እንደ ትምህርት ሊታዩ ይገባል፤ እንደ ሳይንሳዊ ፈጠራ ሊታዩ ይገባል፡፡ ቀላል ማሽኖች እንደ ኢንዱስትሪ መነሻ መታየት አለባቸው። በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ መካተት አለባቸው፡፡ በልማዳዊ መንገድ የሚሰሩ የአካባቢ ሰዎች ልክ እንደ ፊዚክስ መምህር መማሪያ ክፍል ውስጥ ገብተው ልምዳቸው ማካፈል አለባቸው፡፡ የመማሪያ መጻሕፍት ላይ ምሳሌ የሚሰጠው በአካባቢ ያሉ ነገሮችን ነው፡፡ ስለዚህ እነዚያን ነገሮች በተግባር የሚሰሩ ሰዎች ልምድ ቢያካፍሉ፣ ትምህርት ቢሰጡ ምን ችግር አለው?

የእጅ ሙያ ያላቸው ተማሪዎች ልክ ከፍተኛ ቁጥር አምጥቶ እንደሚሸለመው ተማሪ መሸለምና መበረታታት አለባቸው፡፡ ያኔ ሙያውም ክብር ያገኛል፤ ሥራውን የሚለማመዱ ተማሪዎችም ይፈጠራሉ፡፡ ፊዚክስ ከ100/100 ካመጣ ተማሪ ይልቅ አንድ ቀላል ማሽን የሰራ ተማሪ ለፊዚክስ ትምህርት ይቀርባል ማለት ነው፡፡ የእጅ ሙያ ውጤቶች የሳይንስ መነሻ ናቸውና ትኩረት ይሰጣቸው!

# ዓለም አቀፍ

## የሀሰን ናስራላህ ግድያ ፍትሐዊ መሆኑን ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ተናገሩ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የሀሰን ናስራላህ ግድያ ፍትሐዊ መሆኑን ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ተናገሩ፡፡

እስራኤል ባሳለፍነው አርብ ሌሊት በቤሩት በፈጸመችው ጥቃት የሊብኖሱ ሄዝቦላህ መሪ ሼክ ሀሰን ናስራላህን መግደሏ ይታወሳል።

የሄዝቦላህ መሪው ሀሰን ናስራላህ እስራኤል በቤሩት በፈጸመችው ጥቃት መገደላቸውን ባወጣው መግለጫ አረጋገጧል።

በርካታ ሀገራት እና መሪዎች በሀሰን ናስራላህ ግድያ ዙሪያ አስተያየታቸውን እየሰጡ ሲሆን የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ግድያው ለዓመታት በንጹሃን ላይ ለደረሱ ጥቃቶች ፍትህ ሲባል የጠፈጸመ ነው ብለውታል፡ ፡

ፕሬዝዳንቱ አክለውም ሀሰን ናስራላህ አሜሪካዊያንን ጨምሮ እስራኤላዊያን እና ሊባኖሲያዊያን ንጹሃን ዜጎች እንዲገደሉ ምክንያት ነበር ሲሉም ተናግረዋል፡፡

እስራኤል ራሷን የመከላከል መብት አላት ያሉት ፕሬዝዳንት ባይደን አሜሪካ እስራኤል ራሷን ከሐማስ፣ ሂዝቦላህ እና ሁቲ ጥቃቶች መከላከል የምትችልበት ቁመና እንዲኖራት ወታደራዊ ድጋፍ እንደሚያደርጉም ገልጸዋል፡፡

በመካከለኛው ምስራቅ ያለው ሁኔታ እንዳይባባስ የአሜሪካ ጦር ዝግጁ እንዲሆን የመከላከያ ሚኒስትራቸውን እንዳዘዙም ፕሬዝዳንት ባይደን ተናግረዋል ሲል ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

በሊባኖስ ያሉ የአሜሪካ ኢምባሲ ሰራተኞች ከቤሩት ያስወጣች ሲሆን አሜሪካዊያን ሀገሪቱን በፍጥነት ለቀው እንዲወጡም አሳስባለች፡፡



ይህ በዚህ እንዳለ የሂዝቢላህ ደጋፊ የሆነችው ኢራን እስራኤል ሀሰን ናስራላህን እንድትገድል ይሁንታ መስጠቷን አስታውቃለች፡፡

የኢራን ፕሬዝዳንት ማስኡድ ፔዜሽኪያን በግድያው ዙሪያ በሰጡት አስተያየት አሜሪካ በሀሰን ናስራላህ ግድያ ከሀላፊነት መሸሽ አትችልም ብለዋል፡፡



## አሜሪካ ሻህራም ፑርሳፊን ለጠቆማት 20 ሚሊዮን ዶላር እንደምትከፍል ገለጸች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አሜሪካ ሻህራም ፑርሳፊን ለጠቆማት 20 ሚሊዮን ዶላር እንደምትከፍል ገለጸች።

የዓለማችን ልዕለ ሀያል ሀገር የሆነችው አሜሪካ ሻህራም ፑርሳፊ የተባለውን ግለሰብ ለጠቆማት 20 ሚሊዮን ዶላር እንደምትሰጥ አስታውቃለች።

ሻህራም ፑርሳፊ የኢራን አብዮታዊ ዘብ ጦር አባል ሲሆን፤ የአሜሪካ ባለስልጣናትን ለመግደል በማሴር ላይ መሆኑ ተገልጿል።

እንደ አሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት ማስታወቂያ ከሆነ ሻህራም ፑርሳፊ ዋና ተፈላጊ ሰው ሲሆን፤ በተለይም የቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የደህንነት አማካሪ የሆኑት ጆን ቦልተንን ለመግደል የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ተደርሶበታል ተብሏል።

መህዲ ሪዛዪ እና ሻሂን ፑርባክሽ የሚሉ ስሞች እንዳሉትም የሚጠራው ይህ ኢራናዊ ጆን ቦልተንን የሚገድል ሰው በመመልመል እና ተልዕኮውን ለፈጸመ ሰው 300 ሺህ ዶላር እንደሚከፍል እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ እንደተደረሰበት ተገልጿል።

ሻህራም ፑርሳፊ በተለይም በፈረንጆቹ 2021 እና 22 ዓመት ላይ በጡረታ ላይ ያሉት ጆን ቦልተንን ለመግደል የገንዘብ እና የቁሳቁስ ድጋፍ ሲያደርግ ተገኝቷል ተብሏል።

አሜሪካ ይህንን ሰው ያለበትን ያየ ወይም ለጠቆመኝ 20 ሚሊዮን ዶላር ወሮታ እንደምትከፍል አስታውቃለች።

ዋሽንግተን ከዚህ በፊት በተመሳሳይ የሂዝቦላህ ኮማንደር የነበረው እና ከሁለት ሳምንት በፊት በእስራኤል ጥቃት በቤሩት ለተገደለው ኢብራሂም አኪልን ለጠቆመኝ ሰባት ሚሊዮን ዶላር እንደምትከፍል ገልጻ ነበር።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የብስክሌት ጎዳናዎች ለስፖርት ምን ይፈይዳሉ?

**ዓለማየሁ ግዛው**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ዳር ፕሮጀክቶችን (ኮሪደር ልማትን) በመስራት ከተማዋን ውብና ምቹ የማድረግ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ይህም መንገዶች ለእግረኞችና ተሽከርካሪዎች ምቹ እና ተስማሚ፤ እንዲሁም ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ ማድረግ ችሏል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የብስክሌት መጋለቢያ ጎዳናዎች ትኩረት መሳብ የቻሉና የብስክሌት ስፖርት የልምምድና መወዳደሪያ ስፍራ እጥረትን ይቀርፋሉ ተብሎ ታምኖባቸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ካለው ከፍተኛ የሆነ የትራፊክ ፍሰት እና የሰዎች እንቅስቃሴ የብስክሌት ስፖርትንም ሆነ ሌሎች ጎዳና ላይ የሚካሄዱ ስፖርቶችን ለማዘውተር አመቺ ሁኔታ አልነበረም። የብስክሌት ስፖርትን ብቻ ታሳቢ ያደረገ መጋለቢያ ጎዳና ታሳቢ ባደረገ መልኩ አለመሰራቱ ለዚህ ዋነኛው ምክንያት ነው፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያከናወነ የሚገኘው የኮሪደር ልማት የብስክሌት መጋለቢያ ስፍራን አካቶ እየተሰራ መሆኑ ችግሩን ይቀርፋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የብስክሌት ስፖርትን ያማከለ የመጋለቢያ ጎዳና መሰራቱ በልምምድና ውድድር ቦታ የሚታየውን ተግዳሮት እንደሚቀርፍ የአዲስ አበባ ከተማ ብስክሌት ፌዴሬሽን አስታውቋል፡፡ ፌዴሬሽኑ አዲስ በተሰሩ የከተማዋ ብስክሌት ጎዳናዎች በተለያዩ እድሜ ክልል የሚገኙ ብስክሌተኞችን ጨምሮ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳትፍ ሳምንታዊው የብስክሌት ሽርሽር እያካሄደ ይገኛል፡፡ ይሄ ዘወትር እሁድ የሚያዘጋጀው "ሽርሽር በሳይክል" መርሃግብር የሕብረተሰቡን የብስክሌት እና መንገድ አጠቃቀም ግንዛቤን እንደሚያሳድግም ተገልጿል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ብስክሌት ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ ተረፈ፣ እንደ ፌዴሬሽን ውድድሮች እና ስልጠናዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሰራ ገልጸው፣ ከ2015 ዓ.ም በፊት በነበሩት ወቅቶች የልምምድና ውድድር ቦታዎች ችግር መሆኑን ያስታውሳሉ።



በአዲስ አበባ ኮሪደር የሚካሄደው ሽርሽር በሳይክል ፌስቲቫል፣

አሁን ግን በኮሪዳር ልማት ውስጥ ተካተው የተሰሩት የብስክሌት ጎዳናዎች ለፌዴሬሽኑ ትልቅ ግብዓት ይሆናሉ ብለዋል። ለልምምድና ውድድሮች ረጅም ርቀት መጓዝን የሚያስቀሩና ታዳጊዎች፣ ትልልቅ ስፖርተኞችና ኅብረተሰቡ በየ አከባቢው በአመቺ ግዜ ልምምድ ማድረግ፣ ወደ ትምህርት ቤት፣ ወደ ስራ እና ለመዝናኛም ለመጠቀም መልካም አጋጣሚ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ስፖርተኞች ከመኪና እና እግረኞች ጋር ተጋፍተው ልምምድ ሲያደርጉ የነበረውን ችግር በመቅረፍ እንደዚህ አይነት አገልግሎቶችን በመስጠት ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ብስክሌት ፌዴሬሽን በ2017 ዓ.ም የብስክሌት ጎዳናዎች የመጠበቅና አጠቃቀሙን የማስተማር ግዴታ እንዳለበት ተቋም በሕብረተሰቡ የብስክሌት መንገድ አጠቃቀም ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር እየሰራ መሆኑን ይናገራሉ። ለዚህም የተለያዩ ብስክሌተኞችን በተለያዩ ቀናት እና ሰዓታት ልምምድ፣ የብስክሌት ፌስቲቫል እንዲያቀርቡ እየተደረገ ነው። ብስክሌተኞች እንዲሁም ሕብረተሰቡ ለብስክሌት ስፖርት ብቻ የተሰሩ ጎዳናዎችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ እግረኞች መንገዳቸወን ይዘው እንዲጓዙ የማስተማሩ ስራ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደሚሰራም ይገልጻሉ፡፡

በዚህም በአምስቱም የኮሪደር ልማት ጎዳናዎች የሚካሄደው የብስክሌት ጉዞ እየተለመደ መምጣቱን እንዲሁም ሽርሽሩ የብስክሌት ስፖርት በሕብረተሰቡ ዘንድ ተዘውታሪ እንዲሆን ከማስቻሉ ባሻገር ጤናማ ትውልድ ለመገንባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ጨምረው ይጠቅሳሉ፡፡ በኮሪደር ልማት ጎዳናዎች በሚካሄዱ የብስክሌት ጉዞዎች ታዳጊዎች፣ ወጣቶች፣ እና የስፖርት ቤተሰቦች እየተሳተፉ ሲሆን ተቀባይነቱ እየሰፋ ሊመጣ ችሏል፡፡ ጎዳናዎቹን በብስክሌት ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚጠቀሙ አካላት በመኖራቸው ፌዴሬሽኑ እነዚህን አገልግሎቶች ማስተማሩን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስገንዝበዋል፡፡ በቀጣይም ሕብረተሰቡ በአጠቃቀሙ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖረው ፌስቲቫሎችን፣ ስልጠናዎችን እና ውድድሮችን ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመተባበር ለማዘጋጀት ይሰራል፡፡

በአዲስ አበባ መንገዶች ላይ የሚገነቡት እነዚህ፣ የብስክሌት ጎዳናዎች የትራፊክ መጨናነቅን ከመቀነስም በላይ ለብስክሌት ስፖርተኞችና የሕብረተሰብ ክፍሎች የተመቻቸ ሁኔታን እንደሚፈጥሩ ኃላፊው ያስረዳሉ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ በአምስቱም የብስክሌት ኮሪደሮች ዘወትር እሁድ ሽርሽር በሳይክል ተጠናክሮ እንደሚካሄድም ያመላክታሉ፡፡ የብስክሌት ጎዳናዎቹ አሁን ባላቸው አቋም ለልምምድ የሚሆኑ ሲሆን በከተማዋ ለስፖርቱ እየተሰጠ በሚገኘው ትኩረት ውድድሮችን ለማካሄድ በቀላሉ የሚመቻችበትን ሁኔታ ይፈጥራል። ሕብረተሰቡም ልጆቹን በታዳጊዎች፣ በጤና ቡድኖች፣ ክለቦች፣ በፌስቲቫል፣ ስልጠና እና ውድድር እንዲያሳትፍ የማድረግ እቅድ መኖሩንም ገልጸው፣ መንገዶችን በሚፈለጉ ሰዓት ከሚመለከተው አካል ጋር ምቹ በማድረግ ውድድሮችን እንደሚካሄዱ አስረድተዋል፡፡

ታዳጊዎች በየአከባቢው በሚገኙ የብስክሌት ኮሪደሮች ላይ ልምምዳቸውን እያደረጉ በመሆኑ ጥሩ ውጤት እየታየ መሆኑን እና ብስክሌተኛ በብስክሌት ጎዳና እንዲሁም እግረኛ በእግረኛ ጎዳና እንዲጠቀሙ የሚደረገው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ተስፋ ሰጪ ነው ይላሉ፡፡ የብስክሌት ተጠቃሚነት መዳበር የአየር ብክለትን ከመቀነስ፣ የትራንስፖርት መጨናነቅን ከማስቀረት እንዲሁም ጤናን መጠበቅን እንዲሁም ጥሩ ስፖርተኞችን ለማፍራት የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡ በብስክሌት ስፖርት የሚታወቁት ከተሞች አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ስፖርቱ የተዳከመ ሲሆን አሁን በስፖርቱ የተሻለ እንቅስቃሴ ከሚደረግባቸው ጋር የልምምድ ልውውጦች እየተደረጉ እንደሆነም አብራርተዋል፡፡

ፌዴሬሽኑ በ2017 ዓ.ም የተመረቁ የኮሪደር ልማትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ "ሽርሽር በሳይክል" የሚለውን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ ውድድሮችን፣ ፌስቲቫሎችን፣ ስልጠናዎችን ከደጋፊ አካላት፣ መገናኛ ብዙሃን ጋር በመቀናጀት ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ማቀዱንም አክለዋል፡፡